
# ፋሲካ ማሞ



ታህሳስ ፳፻፫ | ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፯ | በነፃ የሚሠራጭ


የወያኔ ሕገመንግሥት
ይከበር? ወይስ ይቀብር?
ርእሰ አንቀፅ
ገፅ ፪




"ግፍና ግፈኞችን ለማስወገድ፤ ስላም፤ ብልጽግናን፤ ዴሞክራሲንና የሕግ የበላይነትን ለማስፈን በህብረት እንነሳ!!"

ድምፃዊትና ተዋናይ ወይዘሮ ጠለላ ከበደ
በ "የኢትዮጵያውያን ማሕበር በዓለም" ጋባዥነት በኒውዮርክ አሜሪካ በስብዓዊ መብት ዙሪያ በተድረገ ስብሰባ ካደረጉት ንግግር የተወሰደ።

ገፅ ፬



## ጽናት


ትላንትና ገፅ ፫

ነፃ አምድ ገፅ ፯


## በድሬዳዋ ዩንቨርሲቲ ተቃውሞ ተነሳ

በድሬዳዋ ዩንቨርሲት ተቃውሞ ተነስቶ በርካታ ተማሪዎች ታፍሰው ተወሰዱ። በፌደራል ፓሊስ ከፍተኛ ድብደባ ተፈጸመባቸው:: የሞቱም ሊኖሩ ይችላሉ። ተቃውሞው የጀመረው በአካባቢው ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ በ ፲፩ ሰዓት ከ ፴ ላይ ነበር። ተማሪዎቹን ሆድ ያስባሳቸው የምግብ ጥያቄ ነው። በተጨማሪም ግን በዩኒበርሲቲው ውሀ ከጠፋ ሳምንት ሆኖታል። እናም ተማሪዎቹ ምግቡን ጥለው ካፊቴሪያውን ለቀው ሲወጡ የተወሰኑት ድምጽ ማሰማት ጀመሩ። የዩንቨርስቲው ተማሪዎች በጣም ተናደው ስለነበር መንገዱን በድንጋይና በጎማ ዘጉት። ፌደራሎች ላይም ድንጋይ መወርወር ጀመሩ። ፌደራል ፖሊሶችም ተማሪውን ከየምኝታ ክፍሉ ጎትትው እያወጡ እጅግ በአሰቃቂ ሁኔታ ይደበድቡ ጀመር።

በሌላ በኩልም በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ሕዝባዊ ተቃውሞ እየተቀጣጠለ ይገኛል። የእስልምና እምነት ተከታይ ወገኖቻችንም ከ ፲፻፳፫ ቀናት በላይ ያስቆጠረውን ጽናትንና ኢትዮጵያዊ ቆራጥነትን የተላበሰውን ሰላማዊ ትግላቸውን ቀጥለዋል። ከዚህም ጎን ለጎን ወያኔ በእብሪት በክርስትና እምነት ላይ የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነትና አፈና እንደ አቡነ ጴጥሮስ ያሉ የሀይማኖት አባቶችና ምእመናን በአንድነት በመቆም ለመመከት መነሳሳታቸውን የሚደርሱን መረጃዎች ያረጋግጣሉ።

የ ሀገር ቤት የዜና ምንጮቻችን እንደሚዘግቡት ከሆነ የተማሪውንና የተቀረውን የህብረተስብ ክፍል የመብታችን ይከበር ትግል ወያኔ "ፌደራል" ብሎ በሰየማቸው ቅልብ ነፍሰ ገዳዮች ማፈን ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ስለሆነም ሁሉም ኢትዮጵያዊ የበኩሉን አስተዋጽኦ በማድረግ ሀገራችንን ከግፍና ከአፈና ነጻ ለማውጣት በአንድነት ለተቀናጀ ትግል ነገ ዛሬ ሳይል መነሳት እንዳለበት ይነገራል።

## "፲፻፳፫ ቀናት ለእምነት ነጻነት"

የ እስልምና እምነት ተከታይ ወገኖቻችን በአራት ሳምንታት ከፋፍለው ያዘጋጁት እና ካለፈው ሳምንት ዓርብ እለት ጀምሮ እየተዘከረ ያለው የ "፲፻፳፫ ቀናት ለእምነት ነጻነት" የመጀመሪያ ሳምንት የጁማዓ የተቃውሞ መርሃ ግብር በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች ተከናውኗል።

**ያቀረብነው ጥያቄ ይመለስ!**
**የእስልምና እምነት ተከታዮች ያልመረጡት አዲሱ መጅሊስ ይበተን!**
**የታሰሩት መሪዎቻችን ይፈቱ! ዋ! ዋ! ዋ!**

በማለት በአዲስ አበባ አንዋር መስጊድ የተደረገው ተቃውሞ በተመሳሳይ ሰአት በሰበታ፤ በአዳማ፤ በደሴ፤ በወልዲያ፤ በሐረር፤ በድሬዳዋ፤ በጅማ፤ በወልቂጤ፤ እና በሌሎች ከተሞችም መከናወኑን ተከትሎ በወያኔ ባለስልጣናት ትእዛዝ የኃይል እርምጃ እስከ መውሰድ መደረሱንም ከደረሰን ጥቆማ ለማረጋገጥ ተችሏል። በዚሁ ተቃውሞ በሐረር ከተማ በወያኔ ከተገደሉት መሀከል አንደኛዋ የስባት ዓመት ህጻን የክርስትና እምነት ተከታይ ስትሆን እናትየውም ልጃቸውን ለማዳን እየሮጡ እያሉ በጥይት ተመትተው ከፍትኛ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን የደረሰን ጥቆማ ያመለክታል። በደሴ ከተማ ኢማሞች በወያኔ ታፍሰው ወዳልታወቀ ቦታ ቢወሰዱም ሕዝቡ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ተቃውሞውን ከእለት ወደእለት እያጠናከረ መሄዱንና በየቦታው በተበተኑ ወረቀቶችም ለበለጠ መስዋእትነት እየተዘጋጀ መሆኑን ምንጮቻችን ዘግበዋል።

## አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ

ወያኔ ዛሬም እንደትላንት ኢትዮጵያን ለማጥፋትና የአፈና እድሜውን ለማራዘም ተማሪዎችን እርስ በርስ የማጋጨት እኩይ ተግባሩን ቀጥሏል። በአራት ኪሎ ዩንቨርስቲ ግቢ ውስጥ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆችን የሚያንቋሽሽ ፅሁፍ

ወደ ገፅ ፬ ዞሯል

## የወያኔ ምርጫ ቦርድ

የወያኔ ጉዳይ አስፈጻሚ ተቁዋም በሆነው ምርጫ ቦርድ እና በ ፳፻፫ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መሀከል የተጀመረው ውዝግብ ወደ ተካረረ ሁኔታ እይተለወጠ መምጣቱን ከሰሞኑ የደረሰን ጥቆማ አጋለጠ። የ ወያኔ ምርጫ ቦርድ ነፃና ገለልተኛ አይደለም እየተባለ ሲተች የነበረውን ሲያጣጥል እና ሲያስተባብል ቢቆይም ሰሞኑን የቦርዱ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆነችው ሰው የወያኔ ከፍተኛ የአመራር አባል መሆንዋን የሚያረጋግጥ ሰንድ መገኘቱ ታውቋል።

## የአዲስ አበባ ከተማ ባለስልጣናት ምንጠራ ተጧጡፏል፤

ሰሞኑን የአዲስ አበባ ከተማ የክፍለ ከተማ ባለስልጣናት ከየቦታቸው ተነስተው እየተንሳፈፉ ከመሆኑም በተጨማሪ የአዲስ አበባ ከተማ የቢሮ ኃላፊዎችም ጭምር እየተነሱ እና የቁም እስር ላይ እንደሚገኙ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ አጋልጧል። ኩማ ደመቅሳም ጥያቄ ምልክት ውስጥ ወድቋል ተባለ። የአዲስ አበባ ከተማ የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን የነበረው የኦህዴዱ ቃሲም ፊጤ በወያኔ ከተጠቁት መሀከል አንዱ ሲሆን በቁም እስር ላይ እንዲቆይ መደረጉንም ምንጮቹ ጨምረው አረጋግጠዋል።

ኦህዴድን ገዝግዞ ለመጣል እየተደረገ ያለው ዘመቻ ከመቼውም ግዜ በላይ ተጠናክሮ ቀጥሏል ያሉት ምንጮች የሲቭል ሰርቢስ ሚኒስትሩ ጁኔዲ ሳዶ ከኦህዴድ ስራ አስፈጻሚነት ከተነሳ እና የሚኒስትርነቱን ቦታ ከተቀማ በሁዋላ ለህክምና ወደ ውጭ ሀገር የተጓዘ ሲሆን የእሱንም የምክር ቤት አባልነት አንስተው ያለ መከሰስ መብቱን ገፍፈው ወደ እስር ቤት ለመወርወር ያቀዱት ሀሳብ በአባ ዱላ ገመዳ ተቃውሞ እንደቀረ ጠቁመው ይህም በወያኔ ቡድን ውስጥ ክፍፍል እንዳለ በይፋ ያጋለጠ ነው ሲሉ ምንጮቹ አብራርተዋል።

## ትውስት

"ሆነ አልሆነ ብሎ ይጨነቃል ዓለም፤
ከትግል የበለጠ ኩቶ አንዳች የለም።
መቻል ብሎ ነገር አንገት መድፋት ጣጣ፤
ለኛስ አይበጀንም ትግላችን ቀን ያውጣ።
ማስወገድ እንጅ ነው መከላት ገዳይን፤
አላስኖር አላስቀምጥ ያለ ሰው በላን።"

(ትንሽ ግጥም ለጆሮ የምትጥም)

**ደረጀ**(በወያኔ በግፍ የተገደለ)







# ኢትዮጵያ

**በኢሕአፓ የዲሲና አካባቢው ደጋፊ አካል**

**የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ**

አድራሻ 5309 Georgia Ave. NW. 2nd fl. Washington DC 20011

ስ/ቁ 202 291 4217

ኢ.ሜል dc.region.eprp@gmail.com


## ርዕሰ አንቀጽ

### የወያኔ ሕገ መንግሥት ፤ ይከበር?!..ወይስ ይቀበር!?

አዲሱን ወያኔያዊ የምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር የሥራ መደብና የሁለቱን ምክትል ሚኒስትሮች ሹመት ተንተርሶ ብዥታ የተጠናወተዉ አንድ መሟገቻ ሰሞነኛ ጫጫታ ሆኖ ከርሟል ። በኢትዮጵያዊነት የምንመካባቸዉን እሴቶች ሁሉ መዛበቻ በማድረግ ልማዱ ገፍቶበት፤ የአገሪቱን ብሔራዊ ቋንቋ በሚመለከት ጋጠወጥነቱን ደጋግሞ ያስመሰከረዉ ወያኔ ፤ የአሁኑን የሥልጣን ሻሞዉን "ክላስተር" በሚል ባዕድ ቃል ፈርጆ አስተዋዉቆታል።
አንድ ቱባ የወያኔ የደኅንነት መዋቅር ሀላፊና በሥርዓቱ ዉስጥ የማይታወቀዉን መድልዎ-የለሽ የብሔር ተዋጽዖ እንዲያመላከት የታከለ አንድ ሌላ ገባር ወያኔ ተደልድለዋል። ዘር እና ለሥርዓቱ ያለ ታማኝነት እንጂ እዉቀትና የሙያ ብቃት ለወያኔ ሹመት መለኪያ ሆነዉ እያዉቁምና ምደባ ሹሙቱ ማንንም ሊያስደንቅ ባልተገባ ነበር። ይሁን እንጂ፤ የወያኔዉን ሹመት ምደባ ተከትሎ ከተቃዋሚዉ የቀረበ ነዉ ተብሎ የሚስተጋባዉ፤ "ህገ መንግሥቱ ተጣሰ" የሚል ጩኸት እስከዛሬም አልበረደም።

ጩኸቱን ተመርኩዞም ሕገ መንግሥቱ እንዲከበር የሚያሳስብ የተማጽኖ ጥሪ ደጋግሞ ተላልፏል። ወያኔያዊዉ አገዛዝ በእስከዛሬዉ ዕድሜዉ የሚያከብረዉ መርህ የሌለዉ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በህልዉናዉ ላይ አደጋ እስካንዣበበ ድረስ የማይሰርዘዉ አንቀጽ ፤ የማይደልዘዉ ሰነድና የማይጨፈልቀዉ ሕግ አለመኖሩን ደጋግመን አይተናልና ጥሪውና ጩኸቱ አስተዛዛቢ ከመሆን አያልፉም። የወያኔ ሕገ መንግሥት ለታተመበት ወረቀትና ቀለም ከወጣዉ ወጪ አንጻር ሲሰላ ዋጋ ቢስ ተደርጎ የመቆጠሩ ምስጢርም ይኼዉ ነዉ።

በሌላ መልኩ ደግሞ ሕገ መንግሥቱ፤ ወያኔ እንደ አገዛዝ ራሱን ለመትከልና ጸረ-ኢትዮጵያና ዘረኛ ድርጅታዊ መርሃ ግብሮቹንና መመሪያዎቹን በብሔራዊ ደረጃ ለመተግበር ህጋዊ መሠረት ያገኘበት ሰነድ መሆኑ ግልጽ ነዉ። ለገሰ ዜናዊ፤ ሕገ መንግሥቱን መንካት፤ ከበሬዉ ራሱ ጾጉር መንጩት መሆኑን ደጋግሞ ሲናገር መደመጡ ያለ ምክንያት አልነበረም። ኢትዮጵያ ሰሜናዊዉን ግዛቷንና ለባህር በር ተጠቃሚነት ያላትን መብት የተነጠቀችዉ በዚሁ ሕገ መንግሥት ተብዬ የወያኔ ሠነድ ምርኩዝነት ነዉ። የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፴፱ም ኢትዮጵያዉያን ለሀገራቸዉና ለአንድነታቸዉ ያላቸዉን ፍቅርና ስሱነት መያዣ በማድረግ ሕዝቡም ሆነ አገሪቱ ለመጪዎቹ ዘመናት ከወያኔ የባርነት ቀንበር እንዳያመልጡ የተዘጋጀ ወጥመድ ነዉ። የኢትዮጵያ ደህንነትና የሕዝቧ ነጻነት ወያኔ ራዕዮቼ ናቸዉ ብሎ በድብቁ ካሰፈራቸዉ ዕቅዶቹ ጋር ከጥንስስ እንስቶ የተፋቱ ናቸዉ። በመሆኑም ወያኔያዊዉ አገዛዝ ሲናድ፤ "ሕገ መንግሥት" ተብሎ የሚጠራዉ የዜጎች የባርነት ሰነድም ሕጋዊ መሠረቱን ማጣቱ እዉነት ነዉ። ሕገ መንግሥቱ የተናደ ዕለትም የወያኔ መንግሥታዊ ህልዉና ያከትምለታል።

ኢትዮጵያዉያን ፤ "ሕገ መንግሥቱ ይከበር!" በሚል ፤ የወያኔን አገዛዝ የከርሞ ዘለቄታ ለመማጠን የሚደረገዉን አዘናጊ ጫጫታ ለማዳመጥ ትዕግስታቸዉ ተሟጧል። ከእስከዛሬዉ ተምረን፤ ለቀጣዩ ዘመናችን ስምረት ወያኔም ሆነ አገዛዙ የተመሠረተበትና በሕዝብ ላይ በኃይል የተጫነበት ሰነድ የሚወገዱበትን ስልት ነድፎ መታገል ጊዜ የማይሰጠዉ ተግባር ነዉ።

**ሕዝባዊዉ ዴሞክራሲያዊ ትግል ያቸንፋል!**

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!**

ዳኔል አበራ

## ደብዳቤዎች

### የጥያቄና መልስ አምድ

ውድ የኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች እንደምን ሰነበታችህ? እኔ ይህን ጋዜጣ በተከታታይ ደርሶኝ አንብቤአለሁኝ። በመልከቱም ረክቻለሁኝ። በርቱ! የኢሕአፓ አመራር የሆኑት አቶ ኢያሱ አለማየሁ ለኢሳት ሬዲዮ የሰጡትን ቃለመጠይቅም አዳምጫለሁኝ። በዚህ ቃለመጠይቅ አቶ ኢያሱ ለበርካታ ጥያቄዎች መልስ የሰጡ ስለሆነ፤ የዚህን ቃለመጠይቅ ፍሬ ሀሳብ በዚህ ጋዜጣ ለአንባቢያን ብታቀርቡ መልካም ነው እላለሁኝ። እናንተም የጥያቄና መልስ አምድ ቢኖራችሁ መልካም ነው።

አሰግድ

**(ከዳላስ)**

### ውድ ዳናኤል!

ውድ ዳንኤል አበራ በቁጥር ፫ ጋዜጣችን ላይ ያወጣነውን ምስል በተመለከተ ስለሰጡን ገምቢ አስተያየት እናመሰግናለን።

**(ከኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች)**

### መምህር የኔ ሰው ገብሬ

ባለፈው እትምችሁ በደብረ ሃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስትያን የመምህር የኔስው ገብሬን መታሰብያ አስመልክቶ የጻፋችሁትን አንብቤዋለሁ። እግዛብሔር ይስጣችሁ። በዚህ አጋጣሚ የቤተክርስትያኑ ምእመናን እና ስራ አስፈጻሚ አባላት ላሳዩት የሐገርና የወገን ተቆርቋሪነት ፈጣሪ አምላካችን እድሜና ጤና ሰጥቶ ለነጻነት ቀን ያበቃቸው ዘንድ የዘወትር ጸሎቴ መሆኑን መግለጽ እወዳለሁ።

ፍቅረ ማርይም

**(ከሜሪላንድ)**

### ውድ የኢትዮያ አዘጋጆች

በየቦታው እየተካሄደ ያለውን የሕዝብ ተጋድሎ በመዘገብና የትግል አቅጣጫ በመጠቆም እያደረጋችሁ ያላችሁትን አስተዋጽኦ አጠናክራችሁ ግፋበት። ድላችን ቀርቧል። የጥቂት ዘረኛ ነፍሰ ገዳዮች የስልጣን እድሜ አጭር ነው። የወያኔ ፈደራሎች ግፍና ጭፍጨፋ የሕዝብን ሀይል አይገታም!

ታገል

**(ከኮምቦልቻ ወሎ)**

### አቶ ኢያሱ አለማየሁ

ለ እሳት በሰጡት ቃለ መጠይቅ ለዘመናት በፋሺስት ደርግና ባንዳዎች እንዲሁም በወያኔ እየተነዛ ያለውን የሃሰት ክምር እንደጉም ሲበትኑት ማድመጥ እንደምን ያረካል! እውነትና ንጋት እያደረ ይጠራል ቢሆንም ለሕዝብና ለሐገር ጠላት ግዜ መስጠት አያሻም! ስለሆነም በያሉበት ለፍርድ ማቅረብ ተገቢ ይመስለኛል። እናንተም በጋዜጣችሁ ሃስትን በእውነት ያለማስለስ መመከት ይገባችኋል ብዬ አምናለሁ። በርቱ።

ደምመላሽ

**(ከአዲስ አበባ)**

### ማስፈረፊያ ይሆን?

በመጀመርያ እንኳን ለጌታችን ለመድሃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል አደረሳችሁ እያልኩ ወደተነሳሁበት ቁምነገሬ ልዝለቅ። በአሁኑ ወቅት አገራችን ኢትዮጵያ በከፋ የችግር ማጥ ውስጥ ተዘፍቃ እያለች፣ የወያኔ መንግስት ግን በዚህ ችጋርና በሽታ ባደቀቀው ሕዝብ ልይ የተለያዩ ረብ የለሽ አዋጆችንና መግለጫዎችን በሕዝቡ ላይ ሲይስግተለትል ይደመጣል። ታዲያ "እየዬ ሲዳላ ነውና" ወያኔ በነዋሪዎቹ ሕዝቦች ላይ የሚያወጣቸው የምን ቸገረኝ አዋጅ ተብዬዎች "የበሰበሰ ዝናብ ስይፈራም" እያስብለው ይሆን?

በእድሉ

**(ከመሪላንድ)**

እንኳን አብሮ አደረሰን። መልካም ታዝበዋል። እኛም የምንለው ይኸው ንው።

የኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች


**ለስራ ፈላጊዎች:**

የ **HESS** ጋዝ ማደያ ገንዘብ ተቀባይ ይፈልጋል።

አድራሻ: **9142 Richmond hwy**

**Fort Belovir ,22060**

**Phone: (202) 415-1764**

## ዜና ከተባለ

**"ሁሉ ሆኖ ቃልቻ ማን ይሽከም ስልቻ"**

በወቅታዊው እንነሳ ካልን እየተካሄደ ያለው የድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ትግል የሚያበረታታ ሆኖ ይገኛል። ስለ ትግል ግንዛቤ ካለን የሕዝብ ትግል ሲነሳ ገና ከጠዋቱ መሰረታዊ የፖለቲካንና የስልጣን ጥያቄ ይዞ የሚነሳ ላይሆን ይችላል። የየራስ ጥያቄዎች ግን አሰባሳቢ ካላቸውና ማዕከል ካገኙ ሊቀናጁና ለመሰረታዊ ለውጥ ምክንያት ወይም ማቀጣጠያ ሊሆኑን ይችላሉ። የድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ምግባችውንና ሁኔታቸውን በተመለከተ የጀመሩትን ተቃውሞ ፌዴራል ፖሊስ በሀይል ለማፈን ያደረገው ዘመቻ ችግሩን አባባሰው እንጂ አላበረደውም። ተማሪዎች ተገድለዋል፤ ታስረው ተደብደዋል፤ ቆስለዋል። ይህንን ስንጽፍ ዛሬ ወያኔ ሕዝብን በተለይም ወጣቱን ከፋፍሎ እንዳለ መገንዘብን የግድ ይለናል። ይህን በተመለከተ የቀድሞውን ተመክሮ ስናይ በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ደረጃ ትግላቸውን ሊያቀናጅ የሚችል ብሔራዊ የኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲዎች ማህበር ነበር። በአዲስ አበባ ደረጃም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲዎች ማህበር ነበር። እነዚህ ተቋሞች ለትግሉ ቅንብርና መጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። በዚህና በዚያ የሚፈነዳውን ቀቃውሞ ዛሬ ወያኔ ሊያጠቃውና ሊያፍነው የቻለው በተናጠል ሊገኝ በመቻሉ ነው። ወያኔ ተማሪውን በብሔረስብ ደረጃ ከፋፍሏል። የጋራ ኢትዮጵያዊ ግንዛቤ ሆነ ድርጅታዊ ይዘት ሊኖራችው ገና አልቻለም። ለዚህም ነው ዛሬ ፍንዳታዎች በየፊናችው የሆኑት። ትላንት በአዲስ አበባ፤ በጎንደር፤ በጂማ ዛሬ በድሬዳዋ በተናጠል። ሙስሊም ኢትዮጵያውያንም በየሳምንቱ ዓርብ ሲሰለፉ ከሌላው የሕብረተሰበ ክፍል የደጋፊው ቁጥር አሁንም አሳዛኝ ነው። አብሮ ተባብሮ መታገል ለመቻል መጣሩ ወሳኝ ነው። የወጣቶች ሚና ከፍተኛ ነውና ተማሪዎች በኢትዮጵያ ደረጃ ትግላቸውን ማቀናጀት መቻል አለባቸው። ማዕከልና አደራጅ መኖር አለበት። ሌላ አማራጭ የለም። ይህን አሌ ብለው ሌላ መንገድ ፈላጊዎች በከንቱ የሚባዝኑና ትግሉንም የሚያዳክሙ ናችው። ወደዱም ጠሉም። ፈለጉም አልፈለጉም። ወያኔ ወጣቱን በብሔረሰብና በሀይማኖት ሊከፋፍል ሲጥርም ያውቁ የነቁ የመሰላቸው ሌሎች ጠባቦችም በኢትዮጵያዊነት አትሰለፉ ወዘተ በሚል ወጣቱን በመከፋፋል ላይ አሉ። ይህን ሁሉ መታገልና ማሸነፍ ያስፈልጋል። ወያኔ ድርጅቶችንም በስርጎገብና በከሀዲዎች አማካኝነት መሰነጣጠቁ የታየ ነው። በቅርቡ ደግሞ በድርድር ሽፋን በናይሮቢ የኦጋዴን ነጻ አውጪ ነኝ ባዩን ከተጠጋ በኋላ ለሁለት ከፍሎት ስልጣንና ገንዘብ ለሆዴ ያለው ክፍል ወደ አዲስ አበባ ተጉዟል። የኦጋዴን ችግር ግን በዚህ መንገድ የሚፈታ አለመሆኑን መገመት ከባድ አይደለም።

ወያኔ ብዙ ቢጥርም የመጣበት ቀውስ ቀላል አይደለም።
በመለስ ሞት የተነሳም የወያኔ የቆየ ቅራኔ ተባብሷል። በቅርቡ ያደረጉት ዝግ የስራ አስፈጻሚ ስብሰባ ሊያስማማችው አልቻለም። በረከትና የሙስናዋ እቴጌ በአንድ በኩል፤ ዘረኛው አዛውንት ስብሐትና ኣጋሮቹ በሌላ በኩል ሆነው መፋለምን ቀጥለዋል። በመጪው የካቲት መጋቢት ይደረጋል የተባለው የኢሕአዴግ ስብሰባም ውጤቱ ካለፈው በበለጠ ውድቅ ይሆናልም ተብሏል። የይስሙላውን ኃይለማርያም ለሙተካትም አድህኖም ተብዬውና ደብረጽዮን የተባለው ከይሲ እየተገፋፉ ናቸው። አድሃኖም የእቴጌ ሙስና ወዳጅ ሲሆን ደብረጽዮን ደግሞ የወያኔ ድርጅት (ህውሓት) ምክትል ፕረዚዳንት ተብሎ ከተሾመ በኋላ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴርም ተብሎ በአሁኑ ወቅት በጸጥታው፤ በሚዲያው፤ በፋይናንስም ዋና ተቆጣጣሪ ሆኖ እያበጠ በመምጣት ላይ ነው። በዚህ ተባለ በዚያም ግን የሲዳማን ሕዝብ ፊጂ የተባለው ኃይለማርያም ለመጪው የወያኔ የምርጫ ባልት ከደረሰ ከቦታው የሚነሳ መሆኑ ከወዲሁ ይታያል። በመኢአድና ኢሕአፓ ሰርጎ ገቦች ተጠቅቷል የሚባለው ብአዴንና በኦነግ ሰርጎ ገቦች ተዳክሟል የሚባለው ኦሕዴድ በየበኩላቸው በወያኔ ላይ ያላቸውን ቅራኔ ይፋ ማድረግ መጀመራቸው እየተደመጠ ነው። የኦሕዴድ ወጣት ካድሬዎች በተለይ መጫወቻ ሆንን ብለው አምርረው ሲቃወሙ ተሰምተዋል። ገገርው ክፍል በቀውስ ሲጠቃ፤ ሕዝብ በቃኝ መረረኝ ሲል መሰረታዊ ለውጥ ይመጣ ዘንድ ግን የሚታገልና የሚያታግል ድርጅት አስፈላጊ መሆኑን የራሳችንም ሆነ የሌሎች ተመክሮ ያረጋግጣል። አብዮት እንደሚቀለበስም በየካቲት ፲፱፻፷፮፣ በአርብ ሀገሮችም ታይቷል።
ጠንካራ ተቃዋሚ ሀይል ወይም ሀይሎች ሊኖሩ አለመቻላቸውን ደግሞ ሁሉም አውቆ በሆድ ይፍጀው ደረጃ ያልተወው ጉዳይ ነው። ነጋ ጠባ ለነጻነታችን የወራትም ያመትም ቀጠሮ የሚሰጡን ባይጠፉም ከባዶ ወሬነት ማለፍ አልቻለም። ቀደም ሲል ኢአግ በሚል ስም የተጀመረውን የትጥቅ ትግል በፕሮፓጋንዳና በሻጥር ያጠቁት ወያኔዎቹ ሳይሆኑ ጸረ ወያኔ ነን ይሉ የነበሩና ዛሬም የሰሩት የተረሳ መስሏቸው ተቃዋሚው መሀል የሚርመሰመሱ ናቸው። ትግል በተገቢው መንገድ አልተያዘምና ተቃዋሚው መሳቂያ መሳለቂያ መሆኑ የሚካድ አይደለም። ይህን በዚሁ እናሳርገውና ለፍርድ መቅረብ የሚገባው ኮለኔል አለበል ወደ ስዊድን ሄዶ ጥገኝት ከጠየቀ በኋላ ግንቦት ፯ የተባለው ቡድን ህዝባዊ ሀይሎች (ህዝባዊ ሓይልታት?) የተባለ " ጦር " ማቋቋሙን ይፋ አድርጓል። መግለጫው የታጀበው በአርበኞች ግንባር አባሎች ፎቶ በመሆኑ የግንቦቱ ፯ " ጦር " አርበኞች ግንባርን ጠቀለለ ወይ ለሚለው ጥያቄ መሪዎቹ ምላሽ ወይ ማብራሪያ አልሰጡም። ከዚህ ከግንቦት ፯ ድርጅት ወጣን ያሉት ክፍሎች ግን ሁሉም ሀሰት ነው ብለው ይቃረናሉ። ለማንኛውም ግን ግንቦት ፯ ሆን ሌላ ወያኔን ወግቶ የሚያሸንፍልን ከሆነ ደስተኞች ነው የምንሆነው። በተግባር ትግል ግን አልታይ ብሎ በትግል ስም መነገድ በዝቶ ነው ስሜታችን የተነካው። እላይን ብዬ አለ ኣርሶ ኣደር የተባለውን ያስታውሰናል። አልፎም ከማን ጋር አብሮ ማንን መውጋት የሚለውም የሚጠየቅ ነው።
ውሃ በለዘብታ እሳት ይፈነቅላል ቢባልም ጭቆናን በረጅሙ በትዕግስት ማስተናገድ ከቶም መቻም አይገባም። ይህን ካልን ዘንዳ የሚከተሉትን እስቲ እናንባቸው፤

- በወያኔ ነጋዴዎች (ካድሬዎች) አማካይነት በጎንደር በኩል (ሑመራን ጨምሮ) ወደ ሱዳን የሀገር ሀብትና ምርት በስፋትና ብዛት በስውር (ኮንትራባንድ) እየተጓጓዘ መሆኑ ተጋልጧል። የቀንድ ከብት፤ ቡና ሰሊጥ፤ ወርቅ፤ ዕጣን፤ የዝሆን ጥርስ ወዘተ በዚህ መንገድ ወደ ሱዳን እየተጓጓዘ ነው ።
- በተሓድሶ ግድብ ሽፋን የተከፈተው የዝርፊያ ዘመቻ ቀጣይ ቢሆንም የግድቡ ሰራተኞች የደሞዝ ጭማሪ ጠየቁ በሚል በርካታ ወታደር ተልኮባቸው ታፍነዋል። ወያኔ በዚያ አካባቢ የሚፈራው እንዳለም በዚሁ ግልጽ አድርጓል። ምን ስንል ደግሞ የግብጽና ሻዕቢያን እጅ እናያለን። ግልገል ግቤ ፫ ን ለማከሸፍ ኬንያ ታጣቂዎችን እያሰማራች ነው የሚባለውንም አቅሎ ማየት አይቻልም ።
- ዛሬ በኢትዮጵያ የኑሮ ውድነት ፴፱ በመቶ ጨምሯል። አንድ ጉርሻም ትርፍራፊ ብር ከሃምሳ ያወጣል። እንደ ወያኔ ጌቶች ምእራባውያን የግፍ ባልት ኢኮኖሚው " ፲፪ በመቶ እያደገ" ነው፡፡
- "የባንዲራና የብሔረሰብ" ቀን በሚል ወያኔ ፲ ቢሊዮን ብር አጠፋም ተብሏል ።
- የ ፳፯ ቢሊዮን ብር ኮንትራት ለወያኔው መስፍን ኢንጂነሪንግ ተሰጥቷል።

ወደ ገፅ ፮ ዞሯል

## ምን ይሰማ ......አገር?



* "በኢትዮጵያ የአንድ ዶላር የምንዛሪ ዋጋ በሁለት ዓመት ጊዜ ዉስጥ ከ ፲% በላይ መዉረዱ ተዘገበ ።"
(ኢሳት ቴቪ በህዳር ፳፫ ቀን ዜናዉ እንዳወጀዉ )

**–** ኢሳቶች የሂሳብ ቅሽምና አለባቸዉ ማለት ነዉ። አለበለዚያ ከወያኔዎቹ ደደብ ኢኮኖሚ ይህን መሰል አሪፍ ዜና ሊመነጭ አይችልም። ....ለመሆኑ ሕዝቡን እያሳወቃችሁ ነዉ እያደነቆራችሁ ?"

* "ስድስት ተማሪዎች በጉብኝት ወደ ናሳ (የአሜሪካ ብሔራዊ የከባቢ አየርና ሕዋ ድርጅት) ተላኩ ።"
(ሪፖርተር ጋዜጣ ፤ ህዳር ፲፱ ቀን ፪፻፬ ዓ.ም )

**–** አባካችሁ ናሳዎች ፤ ተማሪዎቹ ምናልባት ወደመጡበት ሊመለሱ ይፈልጉ ይሆናልና እርቃችሁ አትዉሰዷቸዉ።

* "የእስላም ኢትዮጵያዉያን የትግል ስልት /"
(ፐ/ር መስፍን ወልደ ማርያም ፤ በህዳር ወር በተለያዩ ድረ-ገጾች ያስነበቡት ጽሁፍ ርዕስ )

**–**ምስጋና ይግባችሁ ወንድም/እህት ሙስሊም ኢትዮጵያዉያን፤ ከሕንድ ተሞክሮና ከጋንዲ ጥቅስ ጋጋታ ገላገላችሁን።

* "ፐ/ት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ ለአቡነ መርቆርዮስ ደብዳቤ ጽፈዉ ሠረዙት።"
(ኢትዮ ፎረም ድረ-ገጽ ፤ዲሴምበር ፯ ቀን ፪፻፬ ዓ.ም እንደዘገበዉ )

**–** ባይሰርዙት ነበር ዜናነቱ። "ዉሻዉ ሰዉ ነከሰ ፤" "ሰዉዬዉ ዉሻ ነከሰ፤" ...የትኛዉ ነበር ዜናዉ ?

* "የማይደማመጠው ያ ትውልድ!"
(ታሪኩ አባዶማ፤ ህዳር ፳፻፫ ዓ.ም. በድረ ገጽ ያስነበቡት ርእስ)

**–** ወያኔውም፤የደርግ ባንዳ አስገዳዮችም፤ለሕዝብ ቤዛ ሆነው ከተሰዉት ወጣት አርበኞች ጋር በአንድ ኩታ እየሸበለላችሁ መደማመጥ ከወደ ዬት እንዲመጣላችሁ ትሻላችሁ?

* "አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ለሁለተኛ ጊዜ ተዘረፈ!"
(ሪፖርተር ጋዜጣ የጥቅምት ላይ ዜና")
- ለሁለተኛ ጊዜ፤...ብቻ?!...የዘራፊዎቻችንን ብቃትማ ይህንን ያህል አትዘረጥጡትም። ለማንኛውም ዘራፊውን ለማወቅ ወደ ሰሜን ተመልከቱ። አዲስ ኮሌጅ ሲከፈት ወይም የጥቂት ደልቃቃ ሌቦች ኪስ ሲያብጥ ታገኙታላችሁ።

* "አቶ ሳምሶን (ማሞ) በመመሪያ መፈታታቸውን አመኑ!"
(ጎልጉል ድረ ገጽ፤ ኖቬምበር ፳፫ ቀን ፪፻፬ ዓ.ም.)

**–** ጌታ(ዎቹ)ን የተማመነ በግ ላቱን ከበር ውጭ ያሳድራል" አይደል ብሂሉ?

## ሴቶች ለምን በጾታችን መደራጀት ያስፈልገናል?

(ወይዘሮ ጠለላ ከበደ ታህሳስ ፳፻፫ ኒውዮርክ አሜሪካ)

እኔ የእድሜ ባለጸጋ ነኝ። በመሆኔም በህይወት ዘመኔ ብዙ ነገሮች በግዜ ሲለወጡ መመልከት ችያለሁ። ቀደም ባለው ግዜ ሴት ልጆች ወደ ትምህርት አይሄዱም ነበር። ተወለዱ አደጉ ከዚያ በኋላ ባል ማግባት ልጅ መውለድ፣ ልጅ ማሳደግ፣ ለባላቸው ምግብ ማብሰል ነበር ስራቸው። በኋላ ግን አንድ አንድ ስለትምህርት ጥቅም ያወቁና የመማር እድል ያጋጠማቸው ቤተሰቦች ሴት ልጆቻቸውን ወደትምህርት ቤት እንዲሄዱ አድርገው ነበር። በተለይ በኔ ዘመን የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት ግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ሀይለስላሴ ሴት ልጆቻቸውን ወደትምህርት ቤት እንዲልኩ ለእናትና አባት ትእዛዝ አስተላልፈው ነበር። እኔ በተለይ በሙያዬ ክፍለ ሀገሮችን ዞሬ የማየት እድል በማግኘቴ ሴቶች እህቶቻችን የሚደርስባቸውን ከፍተኛ ድካም መረዳት ችያለሁ። ቀደም ብለው ትምህርትን የቀሰሙ ሴቶች አዲስ አበባ ውስጥ የሴቶች ማህበር ትህምርት ቤት ከፍተው ነበር። እሱም ግርማዊት እቴጌ መነንን ጨምሮ እነ ወይዘሮ ሉሌ ተሰፋዬ፣ ልእልት ሰብለ ደስታ ሌሎችንም ጨምሮ እነኝህን ለምሳሌ ነው የጠቀስኳቸው።

የሰው ልጅ የሰባዊ መብቱ ሲረገጥ፣ የመናገር፣ የመፃፍ የመሰብሰብ መብቱን ሲገፈፍ፣ ላጠፋው ግዜ፣ እውቀትና ጉልበት ተመጣጣኝ ክፍያ ሳያገኝ ሲቀር ወይም የላቡን ፍሬ ሲነጠቅ፣ እንዲሁም በማህበራዊ ህይወቱና በስነልቦናው የሌላው ሰባዊ ፍጡር ተገዥ እንዲሆን ሲገደድ የሕግ የበላይነት ያለመኖርን የፍትህና የዳኝነት መጓደልን የነጻነትና የሙብት መታጣት መኖሩን እንገነዘባለን።

ከዚሁ ጎን ለጎን እኛ ሴቶች ሴት በመሆናችን ብቻ ሌላ ተጨማሪ የግፍ ቀንበር ተሸካሚዎች የነበርንና የሆንን መሆናችን ያደባባይ ሚስጥር ነው። ፍትህና ዴሞክራሲ በሌለበት አገር ዜጎች ለሙብታቸውና ለነፃነታቸው መከበር ሲታገሉ መስዋእት ይሆናሉ:: አሊያም ሀገራቸውን ጥለው ከቤተሰብ፣ ከዘመድ፣ ከነበራቸው ማህበራዊ ትሥሥር ሁሉ ርቀው በመኮብለል እንደወጡ ይቀራሉ:: በስደት ህይወታቸውም ልባቸው ከሀገር አካልቸው በሰው ሀገር ሆኖ ሲዋትቱ በየባዶው ቤት ህይወታቸው አልፎ የሚገኙ ወገኖቻችን ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። በስደቱ ዓለምም ቢሆን በኛ በሴቶች ላይ የሚደርሰው ሥቃይና መከራ እጅጉን የከፋ ነው:: በሊቢያ፣ በሳውዲ አረቢያ፣ እንዲሁም በሌሎች የአረብ አገሮች በሞቀ ውሃና፣ በእሳት እይተጠበሱ፣ ከፎቅ እየተወረወሩ፣ ያለፈቃዳቸው እየተደፈሩ፣ በየበረሀው በአውሬ እየተበሉ፣ በዉሀ ጥም እየተቃጠሉ፣ በየባህሩ ሰምጠው እየቀሩ ወዘተ የሚያልቁ ሴቶች ወገኖቻችን ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ባፍሪካና በላቲን አሜሪካ በረሀዎች ቀልጠው የቀሩትም የሚዘነጉ አይደሉም።

በተለይ ኢትዮጵያዊ ሴቶች ደደቢት ላይ የበቀለው እርጉም የወያኔ መንፈስ በመላው ሀገሪቱ ሰፍኖ ጥቂቶች ሕዝብን በዘርና በሀይማኖት ከፋፍሎ ለማጫረስ ቀን ከሌት ሴራ እየገመዱ ባሉበትና ያገሪቱን ሀብት በብቸኝነት በተቆጣጠሩበት፣ አብዛኛው ሕዝብ ጉርሻ በመግዛት አሊያም ጦሙን በማደር ቀን በሚገፋበት የምድር ሲኦል፣ የሚፈጸመው ግፍና በደል ኢትዮጵያውያኖች እንዲሰደዱ እያስገደደ ነው። እንደፋሽስቱ የደርግ ዘመን ሁሉ ዛሬም በዘመነ ወያኔ እየተፈጸመ ያለው ግፍና በደል፣ የታሪካችን መዋረድ፣ የሰንደቅዓላማችን መሳለቂያ መሆን የመሬታችን ተቆርሶ ለባእድ መሰጠትና ባለ አገሩን ከይዞታው እያፈናቀሉ አባወራውን በሚስቱና በልጆቹ ፊት እያዋረዱ ለም መሬቱን ነጥቀው ለቻይናና ለሕንድ ቱጃሮች አሳልፈው እየሰጡ በማናለኝበት ለሚያደርሱት በደል እንደ የኔሰው ገብሬ ያሉ ቆራጥ ኢትዮጵያውያን ራሳቸውን በእሳት አቃጥለው ዘላለማዊውን የነጻነት ችቦ እንዲለኩሱ አስገድዷል።

በንደዚህ አይነቱ የግፍ ዘመን እኛ ሴቶች እየደረሰብን ያለው ግፍና ስቃይ የሰው ልጅ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ነው። ጨቅላ ልጆቻችን የወያኔ ቅልብ ፌደራሎች ጥይት ሰለባ ሆነው ሲቆጠሩ፣ ወገናችን በጣልያን ፋሺስት እንደተፈጸመው ሁሉ ሬሳው ታስሮ መሬት ለመሬት ሲጓተት፣ በየገዳማቱና አድባራቱ የሃይማኖት አባቶቻችንን እንደ አውሬ ማደኑና መረሸኑ፣ በየመስጊዱ ደጃፍ ወንድሞቻችንን፣ እህቶቻችንን ልጆቻችንን በቅጥረኛ አውሬዎች በጥይት ማስደብደቡ ዘመን የማይሽረው ቁሥል በልባችን እይተከለ ነው። የእምነት ነጻነት በጥቂት የደደቢት እርኩስ አጋንንቶች ተደፍሮ ባለበት በዚህ ዘመን እኛ ሴቶች በትላንቱ የመስዋትነት ታሪካችን ያለፉትን ዛሬም በወያኔ ወሮበሎች እድራሻቸው የተሰወረውን እንደ አበራሽ በርታ ያሉ እህቶቻችንን ፈለግ ተከትለን መብታችንን ለማስከበር፣ ኢትዮጵያችንን ለመታደግ ያላሰለሰ ትግል ይጠብቀናል። ሴቶች የጀግኖች እናት ነን። ሴቶች ሚስቶች ነን። ሴቶች እህቶች ነን። ሴቶች ጓዶች ነን። እንደትናንት ከትናንት ወዲያው ሁሉ፣ እንደ እቴጌ ጣይቱ ነገሮችን ለማቃናት ብልሀቱ፣ ያገርን ጠላት ለመመከት ቆራጥነቱ ተለይቶን አያቅም።

እያት ቅድመ አያቶቻችን ብዙም እድል ያላገኙበትን ትምህርት የመገብየት እድል ያገኘን ሴቶች ሁሉ በከተማም በገጠርም የመማር እድል ላላገኙ እህቶቻችን ተደራጅተን መታገል፣ አይዞአችሁ ማለት ይጠበቅብናል። ዛሬም እንደትናንት እንጨት ሰብረው ውሀ በእንሥራ ተሸክመው ወፍጮ ፈጭተው የእለት ተእለት ህይወታቸውን ለማሸነፍ የሚዋትቱ እህቶቻችን የኛን እገዛ ይሻሉ። ላቅመ ሄዋን ሳይደርሱ ተጠልፈው የሚደፈሩ ሴት ህጻናት፣ በወሊድ ምክኒያት ህይወታችው የሚያልፍ እናቶችና ህጻናት ችግር ሊቀረፍ የሚችለው በወገን ትብብር ነው። ለዚህ ቅዱስ አላማ ደሞ ከኛ ከሴቶች ተደራጅቶ መታገል የበለጠ መፍትሄ የለም።

የመማር እድል ያላገኙ ህጻናት ልጆቻችንና እህቶቻችንን ልንደርስላቸው የምንችለው በዘርና በሀይማኖት ሳንከፋፈል በኢትዮጵያዊነታችንና በጾታችን ተደራጅተን መንቀሳቀሥና መሥራት ስንጀምር ነው። ኢትዮጵያን ካለችበት ማጥ ለማውጣት ልጆችዋን ለመታደግ ከኛ ከሴቶች በላይ ምድራዊ ኀይል የለም። ግፍና ግፈኞችን ለማስወገድ፣ ሰላም፣ ብልፅግናን፣ ዲሞክራሲንና የሕግ የበላይነትን ለማስፈን በሕብረት እንነሳ!!

እናቸንፋለን!!
ኢትዮጵያ ለዘላልም በነፃነት ትኑር!!

## አራት ኪሎ ዩንቨርስቲ

ከ ገፅ ፩ የዞረ

በዩንቨርስቲው ግቢ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ተፅፎ በመገኘቱ ረቡዕ ታህሳስ ፳፫ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም ምሽት ብጥብጡ ሊነሳ እንደቻለ ከስፍራው ከነበሩ የአይን እማኞች የተገኘው ጥቆማ አስረድቷል።

በወቅቱ ከ ፶ በላይ ተማሪዎች ታፍሰው ሲወሰዱ ሁለት የአማራ ብሔር ተወላጆች ብቻ አብረው የተገኙ ሲሆን የተቀሩት ግን ፵፰ቱ በሙሉ የኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎች መሆናቸው ደግሞ የዩንቨርስቲው አመራሮች ሆን ብለው እራሳቸው ያዘጋጁት የብጥብጥ እና የግጭት እቅድ እንደሆነ አመላካች ነው ያሉት ተማሪዎች በድብደባም ከትንዱት መሀከል አብዛኞዎቹ ኦሮሞዎች መሆናቸውን ተናግረዋል።

## ያ ትውልድ ሲታወስ

**(ቁጥር 1)**

ከ ገፅ ፭ የዞረ

እኔም ይህቺን የመታሠቢያ ስንቅ ቋጠርኩለት:

**የተሰካብህ ትጉን ሳይነቀል፣**
**ጽናትህ ሞትን ሳይበቀል፣**
**የሚፈሰው ደምህ ሳይረጋ፣**
**የመሸብህ ቀን ሳይነጋ፣**
**በከፉዎች አካልህ ደቆ፣**
**ሲጋህ ካጥንትህ ለቆ፣**
**የግርፋትህ ሰምበር ሳይሽር፣**
**የገባኸው ወደ መቃብር፣**
**አቤት ስቃይ አቤት መከራ፣**
**የከፈልከው ለዚች ባንዲራ !!!**

**አልረሳውም የመጨረሻ ቃልህን፣**
**የጣር እስትንፋስህን፣**
**ጮክ ብዩ እዘምራለሁ፣**
**ዓላማህን እዘክራለሁ፣**
**ከንቱ አይደለምና ሞትህ፣**
**ለጦቢያ ነው ለእናትህ፣**
**ለፍትህ ነው ለወገንህ ክብር፣**
**የገባኸው ወደመቃብር።**

መታሠቢያ ለመስፍን መሀመድ (ካምቦ)
ተጻፈ ፲፱፻፸፫ አዲስ አበባ
መስፍን መሀመድ ( ከአዶላ ወዩ )

**ድርጅትዎን በኢትዮጵያ ጋዜጣ ያስተዋውቁ**

አድራሻ:- **5309 Georgia Ave. NW**
**Washington DC 20011**
ስልክ ቁጥር:- **(202) 291-4217**
**e-mail:- dc.region.eprp@gmail.com**

# ትላንትና

## መምህር በላይነህ ገ/ማርያም

### በሞቱ ጠላቶቹን ድል የነሳ የኢሕአፓ ኮከብ

(ምንጭ፤ ጎሕ መጽሔት ሚያዝያና ግንቦት ፩ሀየ፺ ዓ.ም)

ካለፈው የቀጠለ

ወሳኝ ለሆን ሌላ ድርጅታዊ ተልዕኮ ተመረጠ ።

"እርምጃ መዉሰድ አለብን በምንልበት ጊዜ እነርሱ እነማን ናቸዉ የሚል ጥያቄ ይነሳል። እነርሱ በደሞዝ ተቀጥረዉ፤ ህዝብ ድርጅት ጽ/ቤት ተቀምጠዉ፤ ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን እየሰበኩ ግን በተቃራኒዉ የሕዝቡን ዴሞክራሲያዊ መብትና የመደራጀት መብት ገፍፈዉ፤ እንደ ኢላአማ ያሉትን የላብ አደሩን የሙያ ድርጅት ዘግተዉና የመምህራን ማህበርን እንዳይሠራ በሰንሰለት አስረዉ፤ የሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴን በትነዉ...የወጣቶች ማህበራትን የአናርኪስቶች መሰብሰቢያ እያሉ ወጣቶችን እያሳደዱ እያሸበሩ በመኖር ላይ የሚገኙትና አንተ እንደዚህ ነህ እያሉ ለማሠራት ባልቻሉት ላይ ርምጃ መዉሰድ ግድ ነበር ።"

መምህር በላይነህ በፍጻሜዉ ሰዓት ለማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ ከሰጠዉ ቃል ተቀንጭቦ የሠፈረዉ ይህ ብያኔ ቀጣዩ የቅጣት በትር የሚያርፍበትን ተረኛ የሚያመለክት ነዉ። ዶ/ር ፍቅሬ መርዕድ ራሱን የመላዉ ኢትዮጵያ ሶሺያሊስት ንቅናቄ ብሎ ይጠራ የነበረዉ የመኢሶን ከፍተኛ የአመራር አካል ሲሆን ከፋሽስታዊዉ ደርግ ጎን በግልጽ ከተሰለፉትና ጸረ-ሕዝብ አቋም ከነበራቸው የወቅቱ ፖለቲካ ፊታዉራሪዎች አንዱ ነበር። በዶ/ር ፍቅሬ ላይ ሊወሰድ ለተወሰነዉ የማስወገድ ርምጃ ከተመረጡት የጥቃት መከላከያ አሃድ አባላት መሀከል ጀግናዉ መምህር በላይነህ ገ/ማርያም ይገኝበታል።

የዶ/ር ፍቅሬን መዉጫ መግቢያና የዘወትር ተለምዶዉን በተመለከተ ቀዳሚዉን ጥናት እንዲያከናዉኑ ለመምህር በላይነህና ለይትባረክ ትዕዛዝ ተላለፈላቸዉ። ሁለቱ ጓዶች ከድርጅታቸዉ በተሰጣቸዉ መመሪያ መሠረት አርንጓዴ ዳትሰን ፒካፕ መኪና በመያዝ ለስምንት ተከታታይ ቀናት ክትትል አደረጉ። ጥናቱ ዶ/ሩ ከሥራ የሚወጣበትን ሰዓት ፤የሚጓዝበትን መንገድ ፤ የሚደርስባቸዉን ሥፍራዎች ፤ ወዘተ አካትቷል። በዚህም መሠረት መምህር በላይነህና ይትባረክ በሰዉዬዉ ላይ ርምጃ ለመዉሰድ ምቹ የሆነዉን ስፍራ ለመወሰን ችለዋል። ዶ/ሩን ለማስወገድ አመቺ ሆኖ የተገኘዉ ደግሞ ባለቤቱን ከሥራ ስትወጣ ጠብቆ በመኪናዉ የሚያሳፍርበት ነበር። እናም ዶ/ሩ ሞርጌጅ ባንክ ሕንጻ ላይ የምትሠራዉን ባለቤቱን ለመቀበል ሲሄድ ጠብቀዉ ተልዕኳቸዉን ለመወጣት ዝግጅታቸዉን አጠናቀቁ ።

ግዳጃቸዉን በሚወጡበት ዕለት ወደ ወሳኙ ተልዕኮ ከመሰማራታቸዉ በፊት ስፕሪንግ ሆቴል ተገናኝተዉ ሻይ ቡና አዘዙ። ያን ዕለት ዶ/ሩን ከቢሮዉ ሲወጣ ጀምሮ መከታተል አላሻቸዉም። ዒላማቸዉ ከቢሮዉ ከወጣ ጥቂት ደቂቃዎች ያለፉት መሆኑን ለማወቅ ሰዓታቸዉን መመልከት ብቻ ይበቃቸዉ ነበር። ሂሳብ ከፍለዉ ከሆቴሉ በመዉጣት ወደመኪናቸዉ አመሩ። መከላከያ ሚኒስቴር ሲደርሱ የዶ/ር ፍቅሬን መኪና ተመለከቷት። ከኋላዉ ሆነዉ ተከተሉት። ከሰንጋ ተራዉ የትራፊክ መብራት አጠገብ እንደደረሱ መምህር በላይነህ ጓደኛዉ ከዚያ እንዲያወርደዉና መኪናዋን መኢሠማ ጽ/ቤት አካባቢ አቁሞ እንዲጠብቀዉ ነገረዉ። ይትባረክም እንደተባለዉ አደረገ።



መምህር በላይነህ ከመኪናዉ ወርዶ እጆቹን ኪሶቹ ዉስጥ በመከተት ከሞርጌጅ ባንክ ፊትለፊት የኮሜርስን ግንብ ጥግ ተከትሎ ወደፊቱ ተረማመደ። የዶ/ር ፍቅሬ ባለቤት ከተለመደዉ ሥፍራ ቆማ ባሏን በመጠባበቅ ላይ ነበረች። ወዲያዉኑም ዶ/ሩ ደረሰና መኪናዉን ወደ ሚስቱ አስጠግቶ አቆመና አሳፈራት። በዚያን ቅጽበት በላይነህ ዶ/ሩ በተቀመጠበት በኩል ወደ መኪናዋ ተጠጋ። ሰላምታ የሚሰጠዉ በማስመሰል የመዘዘዉን ነጥብ ሠላሳ ስምንት ኮልት ሽጉጥ አነጣጥሮ ቃታዉን በመሳብ ጭንቅላቱን በአረር ተረከከለት። ወዲያዉኑም መኪና ይዞ ወደሚጠብቀዉ ይትባረክ በሩጫ ተፈተለከ።

የባሏን በጥይት ተመትቶ መዉደቅ ያስተዋለችዉ የዶ/ሩ ሚስት ከመኪናዉ ወርዳ ልትከተለዉ ሞከራ ነበር። ይሁን እንጂ ፤ትቅርና ባለረዥም ታኮ ጫማይቱ ሴት፤ የባንኩ ጥበቃ ወታደሮች እንኳ ሮጠዉ ሊደርሱበት አልቻሉም። ወደሚጠብቀዉ ጓዱ ደርሶ መኪናዉን ከፍቶ በመግባት በተቻለ ፍጥነት አካባቢዉን ለቅቀዉ እንዲያመልጡ ነገረዉ። ይትባረክም ከመቅጽበት መኪናዉን አስጓርቶ ወደፊት አስዘለላት። የትራፊክ መብራት በማሳበር ከጉምሩክ መ/ቤት በስተኋላ ዞረዉ ሽመጠጡ። ከዚያም መኪናዋን መንገድ ላይ አቁመዉ ወረዱና በእግራቸዉ ይሮጡ ጀመር። መምህር በላይነህ ከባቡር ጣቢያዉ ኋላ ባለዉ ኳስ ሜዳ አቆራርጦ ወደ ጨርቆስ መንደሮች ገባ። ሩጫዉን ለአፍታም ሳይገታ ከዋናዉ የደብረዘይት አዉራ መንገድ ላይ ወጣ። ባገኘዉ ተሽከርካሪ ተሳፍሮ ወደ መኖሪያ ቤቱ አቀና። ቤቱ ሲደርስ ሁሉም ነገር ምንም ነገር ያልተፈጸመ ያህል እማን ነበር።

* * *

የመምህር በላይነህን መጠነ ሰፊ ገድል በዚህን መሰል የጋዜጣ ጽሁፍ ወስኖ ማካተት እጅጉን ያስቸግራል። እርሱ ሕይወቱን ለሚያፈቅረዉ ወገን በቤዛነት አሳልፎ የሰጠ የሕዝብ ልጅ ፤የሕዝብ መምህርም ነበር። ራሱን ዝቅ አድርጎ የተገፊ ወገኖቹን ኑሮ እየኖረ፤ ትግሉን ታግሎለታል። ከላይ የተጠቀሱትን ግዳጆቹን ከተወጣም በኋላ እርፎ አልተቀመጠም። የማስተማር ሥራዉን ሳያስተጓጉል፤ ድርጅቱ ኢሕአፓ የሰጠዉን ተልዕኮ ሁሉ በሙሉ ፍቅር ሲፈጽም ቆይቷል። በወርሐ መስከረም ፩ሀየ፸፱ ዓ.ም ከሰንዳፋ የፖሊስ ኮሌጅ የጦር መሳሪያዎች መዘረፋቸዉን ተከትሎ፤ ድርጅቱ የመምህር በላይነህን መኖሪያ ቤት በጊዜያዊ መሸሸጊያነት የተጠቀመበት መሆኑ በፋሺስታዊዉ የደህንነት ክፍል ታመነበት።

በዚሁም ሳቢያ፤ የፋሽስቱ ደርግ ሰዉ በላ አፋኞች፤ ከሚያስተምርበት ቦታ አፍነዉ ወሰዱት። ባልታወቀ ሥፍራ ለተወሰነ ጊዜ ካቆዩት በኋላ ወደወህኒ ቤት ወረወሩት። በመጨረሻም ለመግለጽ በሚያዳግት ሁኔታ እስከፊ ስቃይንና ስየልን ወደተቀበለበት ማዕከላዊ ምርመራ ወደሚባለዉ የምድር ሲዖል አዛወሩት። በዚያም በሰባት ቁጥር የእስር ክፍል ዉስጥ በፍጻሜዉ በሞት እስከተነዳባት ዕለት ድረስ ቆይቷል ።

**የካቲት ፲፱ ቀን ፩ሀየ፸፱ ዓ.ም፤**

የጠባቡ የሰባት ቁጥር የእስር ክፍል በር ያለወትሮዉ በጊዜ ( ፲፩ ሰዓት ላይ ) ተከረቸመ። ያን መሰሉ ያልተለመደ ሁነት ደግሞ የራሱ የሆነ አንዳች አስደንጋጭ መልዕክት ነበረዉ። እናም እስከዚያኔ በክፍሉ ዉስጥ በመከናወን ላይ በነበረዉ የድራማ ዝግጅት ዘና ፈታ ብሎ የቆዩዉ የእስረኞች ፊት ገጽታ ቅጭም ከስም ብሎ ፍርሃት ይነበብበት ገባ። ሁሉም አንገቱን ደፍቶ የዕለቱ ተረኛ ማን ሊሆን እንደሚችል የየበኩሉን ግምት እያሰላሰለ ይቆዝም ያዘ። በዚህ ጊዜ በአይዞህታና በምክር ጎደኞቹን ሲያበረታታ የነበረዉ ለሁሌዉም የክፍሉ ነፍስ ዘሪ የነበረዉ ጽኑዕ ጓድ ጀግናዉ መምህር በላይነህ ነበር።

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ የእስር ቤቱ ዋና በር ተከፈተ። ቀጥሎም የከባድ መኪናዎች ድምጽ ወደግቢዉ ሲዘልቅ ተሰማ። ከርቀት መሰማት የጀመረዉ የብዙ ወታደሮች የከባድ ጫማ ዳና እየቀረበ...እየቀረበ መጣና፤ ወታደሮቹ ሁሉንም ክፍሎች አልፈዉ ሰባት ቁጥር በር ላይ ሲደርሱ ቆሙ። ክፍሉ ዉስጥ ቀድሞዉኑ ሰፍኖ በነበረዉ ዝምታ ላይ የተነባበረ ታላቅ ጸጥታ ረበበ። በዚያች ቅጽበት እያንዳንዱ እስረኛ ከገዛ ትንፋሹና ከልብ ምቱ በቀር የሚያዳምጠዉ ነገር ከቶ አልነበረም። በጊዜ የተከረቸመዉ የሰባት ቁጥር መዝጊያ ተከፈተ።

ቀድሞ የተጠራው እርሱ ነበር - ታጋዩ፤ ጀግናዉ፤ አስተዋዩ መምህር በላይነህ። የፈሩት መድረሱን እንደተገነዘቡ የክፍሉ እስረኞች ስሙን እየጠሩ መላቀስ ጀመሩ። እርሱ ግን ከቶ አልራደም። የቀረችዉን አንጡራ ሃብት የነተበች ጋቢዉን ለእናቱ እንዲሰጡለት ለጓደኞቹ አስረከበ። እናም **"ድል ለኢሕአፓ!...ኢሕአፓ ያቸንፋል!...ድል ለሕዝባዊዉ ትግል!...ሞት ለፋሺስቶች!"** በማለት ድምጹን ከፍ አድርጎ ፎከረ። እኒያ ደም የጠማቸዉ ወታደሮች ግን አንገቱን አንቀዉ እየጎተቱ አስወጡት። የክፍሉ እስረኞች ዳግም ላይመለስ ከመሀከላቸዉ ለተወሰደዉ ለዚያ የጽናትና የጀግንነት ተምሳሌ በሃዘን በተሰበረ ልብ አነቡለት።

ወታደሮቹ ፤ በጥቂት ደቂቃዎች ልዩነት እየተመላለሱ፤ ሁለት ሌሎች የኢሕአፓ ጀግኖችን ከሰባት ቁጥር ይዘዉ ሄደዋል። ቀጥሎ፤ በዕድሜ አንጋፋዉና በምርመራ ብዙ የተደበደበዉና የተሰቃየዉ **ኢንጂነር ዑስማን** ተጠራ። በጓደኞቹ ድጋፍ ከተቀመጠበት በመነሳት **"ድል ለኢሕአፓ !"** ብሎ እየፎከረ ሳለ ነጥቀዉ እጆቹን ሰባብረዉ ወሰዱት። ከዚያም **ካሱ ኩማን** ጠርተዉ እያዳፉ አስወጡት።

ወደ ገጽ ፮ የዞረ

# ነጻ ሀሳብ

## ምነው ወደ ጭቃው ባትጎትቱን?

ኢትዮጵያውያን በጉድጓድ እሥር ቤት ቢታጨቁ ጠባቂ ዘበኛ እያስፈልጋቸውም ይባላል። በወላጆቻችን ወግ መሰረት ዋርዲያ የሚያስፈልገው አንዱ ተስቦ ሊወጣ ቢጥር ሌሎቹ ጎትተው ይመልሱታል የሚል ነው። ይህ ደግሞ የእግር ጭን ላይ ሰንሰለትና አሎሎ ሆኖ የጎዳንንን ምቀኝነት ይመለከታል። ዛሬም በትግሉ መሥከ ትግልን ለማደናቀፍ ጎታች የሆኑ ኀይሎች ተበራክተዋል። ለምን ብሎ ጥያቄን ወደኋላ እናቆየውና ያለፈን ታሪክ እያነሱ ከዋና ትኩረታችን ሊዘውሩን እየተራወጡ ናቸው።
የእኛና የሕዝብ የትግል ትኩረት ፀረ ወያኔ ነው። ዋናው ጠላት ወያኔ ነውና። ይህ ሀቅ ሆኖ ሳለ ተገቢም ቢሆኑ ዛሬ መለስተኛ የሆኑ ቅራኔዎችን በመያዝ ከዋናው ትኩረት አይታችን እንዲለወጥ ባለመፈለግ የትላንት ወንጀለኞችን ተወት አርገን ቆይተናል። ልንረሳቸው መቼም ከቶም አንችልም። ያፈሰሱት ደም የጓዶቻችንን ነው። የፈጁት ሕዝብን ነው። ግና ደም እያቃገቸው ቢጮሁም በዝምታ ዘግተናቸው በዋናው ጠላት በወያኔ ላይ ማተኮሩን መርጠን ቆይተናል። ሞኝ አሞራ ማደሪያው ዋሻ ይጠፋዋል ነውና እነዚህን ዜጎችም ለምን ፀረ ወያኔ ባዩን መደገፉ ቀና መሆኑን ማስረዳት አይቻልም ወይም ቀላል አይደለም። ወያኔን ትተው በሕዝብ ወዳጆች ላይ ነጋ ጠባ የሚዘምቱ ሁሉ በምንም ደረጃ የሕዝብ ወገን ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም። በጋና፤ በኮንጎ፤ በማሊ፤ በሶማሊያ፤ በሱዳን፤ ወዘተ እየፈሰሰ ያለው አፍሪካዊ ደም ከንቱ አይደለም። ይህን ሀቅ መካድ የሚቻልም የሚያዋጣም አይደለም። ወንጀልና ወንጀለኛ መጠየቅና ሂሳብም ማወራረድ አለባቸው። በዝምታ ሊታለፍ አይችልም። ከፍትህም ከትምህርትም አንጻር ጠቃሚ አይሆንምና።

ይህን ሁሉ እንደመንደርደሪያ ስንወስደው አንድ የቴሌቪዥን ጣቢያና ሌሎችም ሥራዬ ብለው ኢሕአፓን በማጥቃት ዘመቻ ላይ ተሰማርተዋል። ከየቆሻሻ መጣያው ያገኟቸውን ውዳቂዎች እየጠሩና ቃለመጠይቅ እያሉ በማቅረብ ኢሕአፓን በማውገዝና በመወንጀል ላይ ተሰማርተዋል። ግባቸው ምን እንደሆነ የራሳችን ግምት ቢኖረንም ይህ ዘመቻ ለሕዝብ ፀር ወያኔ ትግል እንቅፋት መሆኑ ደግሞ ግልጽ ነው። በቅድሚያ የዘመቻው ፊታውራሪዎች ራሳቸው በወንጀል የተጨማለቁና አሳፋሪ ታሪክ፤ ለፍርድ የሚያቀርብ ታሪክ ያላቸው ናቸው። ነጋ ጠባ መድረክ አገኘን ብለው ወይም ጌታቸው ባዘዛቸው መሰረት በኢሕአፓ ላይ ዘመቻ ሲያካሄዱ ድርጅቱ የዝምታ አቋሙን መቀየር መገደዱ የግድ ይሆናል።

ሕዝብን የፈጁ አረመኔዎችና የቀይ ሽብር ወንጀለኞችን በተመለከተ ኢሕአፓ ስም ዝርዝራቸው በእጁ አለ። ሕዝብን ሽጠው በሚሊዮን ዶላር የተከፈሉት፤ የአባት ስም ስለቀየሩ የተደበቁ የመሰላቸው፤ ለባዕድ ስላደሩ ማንም የሚነካቸው ያልመሰላቸው፤ በቶሮንቶ፤ በዋሽንግተን በቨርጅንያ በዳላስ በአምስተርዳም በፍራንክፈርት በለንደን በደቡብ አፍሪካ በእሽኒያ ያሉትን ነፍሰገዳዮች ሁሉ ከነታሪካቸው እናውቃቸዋለን። እንኳን የቆዩትን የቅርቦቹንም በእነግ ሥር የተሸሸጉትን አረመኔ ሀሰን አሊዋችንም አልረሳናቸውም።

ዋናው ትኩረታችን ግን በወያኔ፤ በዛሬ ላይ በመሆኑ ወደኋላ ተመልሰን የደርግና የቀይ ሽብር ወንጀለኞችን ለማጥቃት ሳንሯሯጥ ትተን ነበር። ግን አላርፍ ያለች ጣት ሆነና ነጋ ጠባ በተለይም በተወሰነ የቴሌቪሽን ጣቢያ አማካይነትና ኢጋፋሪነት ብቅ እያሉ ታሪክን የካደ ዘመቻቸውን ሲከፍቱ በዝምታ ማሳለፉ ሥህተት ሆኖ ይገኛልና የግድ ባንፈልገውም ነፍሰ ገዳይን ነፍሰ ገዳይ ብለን መዝምት እንገደዳለን።

የደርግ ነፍሰ ገዳዮችን ከነዝርያቸውና ከያሉበት መደበቂያ ሁሉ እናውቃቸዋለን። ነግ ታሪካቸውናን ወንጀላቸውን ዘርዝረን በአለምአቀፍ ደረጃም ክስ ልንመሰረትባቸው የምንችል ነን። ማንም የሚያድናቸው አይኖርም። ከነቀልቤሳ እጣ መማር የሚችሉ ናቸው። በየድርጅቱ ስለተደበቁ ማንም የሚነካቸው ያልመሰላቸውም ይሞኛሉ። ለዚህም ነው ወደጭቃው አትጎትቱን፤ በወያኔ ላይ እናተኩር፤ ከነካካችሁን አፀፋውን መልሰን ወደገህነም እንከታችኋለን ማለት የተገደድነው። ኢሕአፓን እየሰደባችሁና እየወነጀላችሁ ያላችሁ ሁሉ ንፁህ ሽማ የላችሁም። የትና መቼ እንደቆሸሻችሁና እንደተጨማለቃችሁ ኢሕአፓ ያውቃል። አላርፍ ካላችሁ ደግሞ ይህን ሁሉ ዘርግፎ የአደባባይ ጉዳይ በማድረግ ራሱን ለመከላከል ይገደዳል። ይህ ታዲያ ያዋጣችኋል?

የኢሕአፓ ዋና ትኩረት ወያኔን በመዋጋት ላይ ነው። ነጋ ጠባ ግን ድርጅቱን በመወንጀልና በመክሰስ ዘመቻ ስምሪቱ ከጦፈ፤ ያውም በራሳቸው በደርግ ወንጀለኞች፤ ኢሕአፓ ታሪክን ከመጠበቅ አንፃር ዘመቻውን ለማክሸፍ መንቀሳቀስ ይገደዳል።

በየስርቻው የተደበቁት የቀይ ሽብር ወንጀለኞች ላይ ሕዝብን ሽጠው በከበሩት ላይ፤ ለባዕድ አድረው ሀገርን በሸጡት ላይ፤ ተቃዋሚ ነን እያሉ ለወያኔ ባደሩት ላይ ወዘተ ያመረረ ዘመቻን ማድረግ ይገደዳል። አላርፍ ያለች ጣት አትሁኑ ብሎም መምከር የሚጥረው ከዋናው ትኩረቱ አዘንፋችሁ በራሳችህ ላይ መርገምን እንዳታመጡ በሚል ነው። ኢሥፓ ሞቷል፤ እንጦሮጦስም ወርዷል። አሌ ብላችሁ ነፍስ ልትዘሩበት የምትሹ ወንጀለኞች ጥረታችሁ ኢሕአፓን በማውገዝ ላይ እስከተመሰረተ ድረስ እንዳለፈው ታግለን ከጥቅም ውጭ እናደርጋችኋለን። መሳሪያ ሆነውም ዘመቻችሁን የሚያጅቡትን አላርፍ ካሉ እንዲሁ ትኩረት ሰጥተን ታግለን የምናከስማቸው ይሆናሉ። ታሪካችንን መጠበቅ ሀገርንም ማስከበር ግዴታ አለብንና ነው። በመቶ ሺ የሚቆጠር ሕዝብን የፈጀ አረመኔ ሊያዳንቁ የተነሱ፤ በኢሕአፓ ላይ ሊዘምቱ መድረክ የሚሰጡአቸው የጸረ ሕዝብ ወንጀል ተባባሪዎች ናቸው። አላርፍ ብለዋልና ከዋነኛው ፀረ ወያኔ ትኩረት ቀነስ አርጎ እነዚህንም ጥግ ማስያዝና ዝም ማሰኘቱ የትግላችን ተልኮ ይሆናል።

በአሜሪካ በአውሮፓ በየቦታው ያላችሁትን ፀር ሕዝቦችና ወንጀለኞች ሁሉ እናውቃችኋለን። በወያኔ ተቀጥራችሁ ታሪክ ብላችሁ ቆሻሻ ጽሁፍ የምታቀርቡትን ሁሉ እንደዚሁ። ለፀረ ኢሕአፓ የቀይ ሽብር ወንጀለኞችና ደርጎች መድረክ የሆነው የቴሌቪዥን ጣቢያ ተው አረፉ ምክርን እንሰጣለን። ሀገራችንን በሚጠቅምና ወያኔን በሚጎዳ ተግባር መሰማራቱ ይበልጥ ለሀገር ይጠቅማል። በታሪክና በደም የቆሸሸ ነጠላውን በሀሰት ታሪክ ልፈፋ ሊያጥብ ለሚጥረው መድረክ መሆኑ እራሱ ወንጀል ነው። በወያኔ ኢጋፋሪነት ዛሬ ስለኢሕአፓ ታሪክ ፀሀፊዎች ፈልተዋል። በዓብዛኛው ማፈሪያ የብእር ቅጥረኞች ናቸው። ታሪክ የሚሉት በአብዛኛው ሀሰት ነው።

ለወያኔ ጫጫታ የሚያመች። ከደምቢያ እስከ ዋሽንግተን አሉ፤ ከናይሮቢ እስከ ቤተመንግሥት አሉ ወዘተ። በኢሕአፓ ውስጥ ይህ ነው የማይባል ሚናና ሚዛን ያልነበራቸው ግብዞች የጫሩት ሁሉ ወያኔአው ተልኮን ከሚሟላት ሌላ ታሪካዊ ሚዛንም ከቶም የላቸውም። በቃለ መጠይቅ አማካኝነት ፀረ ኢሕአፓ ዘመቻን ማጧጧፍ የተያያዙት ከፍሎች መጨረሻቸው ሀፍረት ነው። እውነት አትደብቅምና። በኢሕአፓ በኩል ግን ጥቃቱ በዛሳ ብሎ ፊቱን ወደ መልስ ካተኮረ ለከሳሾቹ የሚበጅ አይሆንም። ትኩረቱን ከወያኔ ላይ አንስቶ በቀይ ሽብር ወንጀለኞች ላይ ካደረገ በየቦታው የተደበቁት በጋለ ምጣድ ላይ የሚጣዱ ይሆናሉ። አላርፍ ካሉ ግን ይህ የሚቀር አይሆንም። በተለይም በእኛ ባሰ ብለው ኢሕአፓን መድረክ አገኘን ብለው ሊወነጅሉ የተነሱትን በተመለከተ አላርፍ ያለች ጣት ማለቱ ተገቢ ይሆናል። ጥቃቱ ሲበዛ ትኩረትን ወደ አጥቂዎቹ ማድረጉ ከባድ አይደለም። ለዚህም ነው በወያኔ ላይ ስናተኩርና ሁሉም ያተኩር ስንል ወደኋላ ወደ ጭቃ አትጎትቱን የምንለው።
የደርግን ፀረ ሕዝብ አረመኔና ፋሽስታዊ የሽብር አገዛዝ የሚያሳምር ቀለም አይኖርምና እርማችሁን አውጡ። ኢትዮጵያውያን ሀገር ወዳዶች እስካሉ ድረስ ኢሥፓ የሚል ከይሲ ተቋም ዳግም ብቅ የሚል አይደለምና እርማችሁን አውጡ። በኢሕአፓ ላይ ዘመቻው ትላንትም አልሰራምና ዛሬም ድርጅቱን የሚያውድም አይሆንምና ቃለ መጠይቅ አድራጊዎች ሆናችሁም መላሾች በሌላ ገንቢ ስራ ብትሰማሩ ይሻላል እንላችኋለን።

እሌ ማለቱ ከበዛ ግን ሁሉንም ፀረ ሕዝብ ኢሕአፓ ለመታገል ዝግጁ መሆኑን ማወቅ ይገባል። ከፊታችን የተደቀነው ፀር ወያኔ ትግል እያለ ወደኋላ በመጎተት ያን አረመኔና ፋሺስት ደርግ ከነርዝራጉዎቹ በትኩረት ታግሎ ባትሉን ይመረጣል። ቦ ጊዜ ለኩሉ።


### ኢትዮጵያ ጋዜጣን

***በተለያዩ ድረ ገጾች**

ሀ. **Eprp.com**

ለ. **Asimba.com**

ሐ. **Debteraw.com** ወዘተ.

***በ Face book**

***በ Email** ማንበብ ይችላሉ


### "ሁሉ ሆኖ ቃልቻ ማን ይሸከም ስልቻ"

ከገፅ ፫ የዞረ

- ወያኔ ሳይንስ አካዳሚ በሚል የራሱ ቅጥረኞች የትምህርት ተቋሙን የሚቆጣጠሩበት አዲስ ተቋም ያቋቋመ ሲሆን የዚህ ረቂቅ የቀረበው ተቃዋሚ ነን ከሚሉና ሀገር ሊመለሱ ከፈለጉ ምሁሮች ነውም ተብሏል።
- በአዲግራት የሙስሊም ኢትዮጵያውያንን የመቃብር ቦታ ያፈረሰ ወያኔ፤ ራሱን ችግርና ቀውስ ውስጥ መክተቱን የአካባቢው ነዋሪዎች አረጋግጠዋል።

የዘመኑ ወሬ ይቀዳል ባቦሬ እንዳንባል እስቲ ቃላችንና ግብራችን ይስሙሩ፤ ይመሳሰሉ። ጦር ያልነውም ጦር እንስብቅ፤ እንወርውር። እንታገል። ቀና ያሰማን ወገኖች።

# መምህር በላይነህ

ከ ገጽ ፫ የዞረ

ከየእስር ከፍሉ የተወሰዱትን በጠቅላላዉ ፵፫ የሚሆኑ እስረኞች አንድ ላይ ሰበሰቧቸዉ።ከዚያም በሁለት ረድፍ በተሰለፉ ወታደሮች መሃከል በማለፍ ወደተዘጋጀላቸዉ ትልቅ ተሽከርካሪ እንዲያመሩ አደረጓቸዉ። ወታደሮቹ በእጆቻቸዉ የኤሌክትሪክ ሽቦ ይዘዋል። እስረኛዉ ገና በአጠገባቸዉ ከማለፉ ከኋላዉ ጠልፈዉ በግንባሩ ይደፉታል። ወዲያዉኑም አንድ ወታደር ዘልሎ ከጀርባዉ ላይ በመዉጣት እንዳይንቀሳቀስ ከመሬት ጋር ሰፍቶ ይይዘዋል። የተቀሩት ወታደሮችም እጆቹ እስኪሰበሩ የኋሊት ጠምዝዘዉ፤ በአፉ ዉስጥ በሚያልፈዉ ሽቦ፤ ወደጀርባዉ ከታጠፉት እግሮቹ ጋር አቆራኝተዉ ይጠፍሩታል። ይህም እስረኛዉ አንዳች አይነት የሰዉነት እንቅስቃሴ ባደረገ ጊዜ ሁሉ ሽቦዉ አፉን እየሰረሰረ...እየሰረሰረ ሥጋዉ ዉስጥ እንዲዘልቅ የሚያስችል ሌላዉ የማሰቃያ ዘዴ ነበር።የእስረኛዉ የእጅ አጥንት በሚሰበርባቸዉ አጋጣሚዎች ደግሞ ሽቦዉ በይበልጥ እየጠበቀ ይሄዳል።

በላይነህና የተቀሩት እስረኞች በዚህ መልክ ከተቆራኙ በኋላ ጌሾ እንደተሞላበት ኩንታል ወደ መኪናዉ እየተወረወሩ ተጫኑ። ጭነቱ እንዳበቃም መኪናዉ ሞተሩን አስጓርቶ በፍጥነት ተፈተለከ፤-የተጫኑት ወጣቶች በጅምላ ተገድለዉ፤ በጅምላ ወደሚቀበሩበት የኮተቤ ጫካ። በዚያን መሰሉ ቅጽበት በመንፈሱም ሆነ በአካሉ ላይ በደረሰበት ሁሉ ሳይበገር፤ ሽንፈትን ሊያሸንፍ፤ እጅ መስጠትን ራሱን እጅ ሊያሰጥ የሚያስችል ስልት ለማዉጠንጠን የሚበቃ አቅም ያለዉ ሰብዐዊ ፍጡር በቁጥር ብዙ አይደለም። መምህር በላይነህ ደግሞ ከነዚሁ ለማመን የሚያዳግት ጀብዱ ከሚያስቆጥሩቱ ጥቂት ልበ ሙሉ ጀግኖች አንዱ ነበርና አደረገዉ።በአፉ ዉስጥ የገባዉን ሽቦ ሲያኝከዉ...ሲያኝከዉ ቆይቶ ቆርጦ በመጣል እግሮቹንና እጆቹን ከእስር ፈትቶ በመነሳት ዙሪያ ገባዉን አማተረ። ሁለት ጂፕ መኪኖች ወደሞት የሚጓዙበትን ተሽከርካሪ በቅርብ ርቀት በመከተል ላይ እንደነበሩ አስተዋለ። በመቀጠል የቅርብ ወዳጁንና የትግል ጓዱን፤ ኢንጂነር ዑስማንን እንደምንም ፈልጎ አገኘዉ። ኢንጂነሩ ግና ዘላለማዊዉን እረፍት አሸልቦ ነበር።

የጓዱን መጨረሻ በዚህ መልኩ የተረዳዉ መምህር በላይነህ ጊዜ አላጠፋም ። ፈቱን ወደ ሌሎቹ እስረኞች በመመለስ ሰባት የሚሆኑትን ከተኮደኮዱበት እስር ፈታቸዉ። ወደ ሞት የሚያጓጉዛቸዉ መኪና መገንጠያ መንገድ ላይ ደርሶ በመጠምዘዝ ላይ ሳለ መምህር በላይነህና ከእስር ያላቀቃቸዉ ሰባት ያህል እስረኞች ከመኪናዉ ዘልለው መዉረድ ጀመሩ።ከኋላቸዉ ይከተሏቸዉ የነበሩት ወታደሮች ሩምታ ተኩስ አወረዱባቸዉ። ከዘለሉት እስረኞች መሃከል ሶስቱ ወዲያዉኑ የተገደሉ ሲሆን መምህር በላይነህ ግን ከለላ ይዞ ከወታደሮቹ ሊያመልጥ ችሏል። ከቅርብ ርቀት ሆኖ ከጥቂት ጊዜ በፊት አብረዉት ሲጓዙ የነበሩት ወጣቶች ሲረሸኑ ተመልክቷል። ያን ሌት ከዚያዉ ጫካ ዉስጥ ተሸሽጎ በማሳለፍ ሊነጋጋ ሲል አካባቢዉን ለቅቆ ተሰወረ።

ለጥቂት ጊዜ ያህል ስፍራ እየቀያየረ ከሰነበተ በኋላ ከአንድ በድርጅታዊ ሥራ ሲቀርበዉ ከነበር ጓደኛዉ ቤት በዘበኛነት ተቀጠረ። ይሁን እንጂ ቤቱ የነበረበት አካባቢ ከማዕከላዊ የወንጀል ምርመራ ብዙም የማይርቅ በመሆኑ ሳቢያ ከቶ ምቾት ሊሰማዉ እንደማይችል ርግጠኛ ነበር።

እናም ደርግ ሁለተኛዉን የመንጥር ዘመቻ ማካሄድ በጀመረበት ወቅት መምህር በላይነህም ተቀጥሮ የሚሠራበትን ቤት ትቶ በመዉጣት እንደገበሬ ለብሶ ራሱን በመቀየር ወደቀድሞ መኖሪያዉ ወደ ኢቃቂ አመራ። በአካባቢዉ በሚገኝ አንድ ዋሻ ዉስጥ ተደብቆ ለጥቂት ቀናት ሰነበተ። ከዕለታት መሃል በአንዱ ግን የአካባቢዉ ገበሬዎች አግኝተዉ ያዙት። የዋሻ ኑሮዉ አበቃና ጠባቂዎቹ ለኢቃቂ እስር ቤት አስረከቡት። ከጥቂት ቀናት ቆይታ በኋላ ቀድሞ ወደነበረበት ማዕከላዊ የወንጀል ምርመራ ተዛወረ። ከጭራቁ ፶ አለቃ ተሾመ ባዩ ጋርም ዳግም ተፋጠጠ። ፶ አለቃዉ ቀደም ብሎ ወደ ሞት የነዳዉን መምህር ዳግም በአካል ቆሞ ሲያየዉ ዐይኖቹን ማመን አልቻለም።

ጉዳዩ ወደ ደርግ ጽ/ቤት ሪፖርት ተደረገ። መምህር በላይነህም ከዚያን ጊዜ በኋላ በደርግ ጥበቃና ቁጥጥር ስር እንዲሆን ተደረገ። በወቅቱ ኢሕአፓን አዉግዞ ከደርግ ጋር እንዲሠራ በተደጋጋሚ ጥያቄ ቀርቦለት ነበር። ይህንን መሰሉን ከህደት ግን የቆራጡ መምህር አዕምሮ ከቶ የሚቀበለው አልነበረም። በትግሉ ጅማሬ ላይ ፍጹም በሆነ እምነት "የትግሉ ነዉ ሕይወቴ" ብሎ በዘመረዉ ሕዝባዊ ቃል ኪዳኑ እንደጸና፤ ሌሎች እያሌ የኢሕአፓ ጀግኖች በተጓዙበት የመስዋዕት ጎዳና እንበለ ፍርሀት ተረማመደ። ለመላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የነበረዉን ፍጹም ፍቅርም በሥጋዊ ሞቱ አረጋገጠ። ክብር ሞቱ ለሰማዕት።

# ያ ትውልድ ሲታወስ
## (ቁጥር 1)

በሚያሳዝን ዝምታችን ውስጥ የቀበርነውን ዕውነተኛ ታሪክ በሞት ሳንቀደም ለባለቤቱ (ለህዝብ) እናቅርብ በማለት አብዱ አብዱላሂ "ያልታደለው ትውልድ" በሚለው መጽሀፍ ውስጥ ያስተላለፈውን የአደራ መልክት ካነበብኩ ጀምሮ በዝምታዬ ውስጥ የነበረውን ዕውነት ለመዘከር የረዥም ጊዜ ህልም ነበረኝ:: ምክንያቱም አብዱ ያስተላለፈው መልክት ትክክል ከመሆኑም በላይ የሰራነው ታሪክ ለህዝብና ለሀገር ነውና መልሰን ለህዝብና ለሀገር ማስቀረት እንዳለብን በፍጹም ልቤ አምናለሁ:: ይህ በእንዲህ እንዳለ በቅርቡ ደግሞ አሲምባ በድኅረ ገጹ ላይ ታሪካችንን ለባለቤቱ እንግለጸው በማለት ደጋግሞ የሚያስተላልፈውን መልክት በማንበቤ የበኩሌን ልተነፍስ ፈለግሁ::

ከነጥላሁን ግዛው መገደል በኋላ በመላው ሀገሪቱ ትምህርት ቤቶች የተነሳው ቁጣ ቋያው እንደሰደድ እሳት ተቀጣጥሎ ቋሚ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ሆነ:: በዚህም ሂደት ውስጥ በየዓመቱ በሚደረገው የነጥላሁን ግዛው ማርታና ዋለልኝ... የሙት ዓመት መታሰቢያን ምክንያት በማድረግ፣ ጸረ ዲሞክራሲ አስተዳደርን በመቃወም ሠላማዊ ሰልፍ ማድረግ ዋናው የትግሉ መንገድ ከመሆኑም ባሻገር በውስጡ ጽሁፎች እና በራሪ ወረቀቶችን በመበተን ህዝቡንና መላውን ወጣት ለትግል በማዘጋጀት ረገድ ተማሪው ቀዳሚውን ሥፍራ ተረከበ:: ሰላማዊ ሰልፎች በሚደረጉበት ጊዜ ሠልፉ በጦር መሳሪያ ተኩስ እስከሚበተን ድረስ መታሠርንና መገረፍን የማይፈራና ደፋር የተማሪዎች ህብረት የተፈጠረበት ጊዜም ተወለደ::

የተማሪውን እንቅስቃሴ ተገቢነትና ለሀገራችን የዲሞክራሲ ለውጥ አስፈላጊነትን በመላው ተማሪ መካከል ቆመው ድምጻቸውን ከፍ አድርገው የሚናገሩና ጽሁፍ የሚያነቡ ወጣቶች በፖሊስ እየታደኑ ወደ እስር ቤት ሲወረወሩ ተማሪው እነሱ እስካልተፈቱ ድረስ ትምህርት አንማርም በማለት በማያቋርጥ አመጽ በወላጆች ኮሚቴ አማካኝነት እንዲፈቱ የቻለበት ጊዜም ቀላል አልነበረም::

እንግዲህ ከዚህ ጀምሮ ነው የተማሪው አንድነትና መጠናከር ከፍ እያለ መምጣት የጀመረው ይሁን እንጂ ሁሉም ተማሪ የፖለቲካውን ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ተረድቶ ነው ለማለት ባያስደፍርም በተማሪው መሀል የነበረው አንድነትና መደጋገፍ ትልቁ የእንቅስቃሴው ጉልበት ሆኖ ቆይቷል:: በተማሪው እንቅስቃሴ በተወለደው ለውጥ ትልቅ አጋጣሚ የተፈጠረለት ደርግ ቀዳሚ እርምጃው በእጁ ያለውን ጠመንጃ ወደ ወጣቱ መተኮስ ብቻ ስለነበረ፣ በፓርቲው (በኢሕአፓ) ማኒፌስቶ ዲሞክራሲያ፣ በተማሪ እንቅስቃሴ መሪዎችና በሀቀኞች አማካኝነት ወጣቱን ቀጥተኛ የፖለቲካው መስመር ላይ እንዲገኝና የእንቅስቃሴውን ግብ እንዲረዳ በማድረግ ከምን ግዜውም በላይ ፈጣን የሆነ ሚስጥራዊ የትግል እንቅስቃሴ ተጀመረ::

የእድገት በህብረት ዘመቻ ዘማቾች በየአካባቢያቸው በሚያደርጉት እንቅስቃሴ በጥቂት ግዜ ውስጥ ወጣቱን የዴሞክራሲ ታጋይ አደረጉት:: የትግሉን መንገድ ይቃኝ የነበረው ወጣት መንገዱን ሲያገኝ ሊያቆመው የሚችል ኃይል አልተገኘም:: በዚህ የትግል ሂደት ውስጥ በሥልጣን ላይ የነበረውን መንግሥት ምግባርና አስተዳደር የተመለከተ ማንም ኢትዮጵያዊ በተለይም ወጣቱ ኃይል ዝምታን ሊመርጥ አልተቻለውምና ትግሉን መረጠ::

ጠንካራውና ከብረት የጠነከረው የኢሕአፓ ዲሲፕሊን ወጣቱን በማህበረሰቡ ዘንድ የተለየ አመለካከት እንዲኖረው አስችሎታል:: በዚህም የተነሳ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ወላጆች የትግሉ ሂደት ተባባሪዎችና አባሎች እንዲሆኑ አስችሏቸዋል:: የህዝብ ድርጅት ጽህፈት ቤት ሲቋቋም ቀዳሚው የድርጅቱ አላማና የድጎማው ለማኝ መሆን የቻሉ፣ ቀድሞውንም የወላዋይነት ሚዛን የነበራቸው አንዳንድ መምህራን እና ተማሪዎች በተማሪዎች ላይ የሚደረገውን ክትትል ለማገዝ ከጽህፈት ቤቱ ጋር ቆሙ:: ይሄኔ ድብብቆሹ ኃይል እያገኘ አፈናና ግድያው የአደባባይ ክንዋኔ እየሆነ መጣ:: የደርግ አረመኔያዊ ጭፍጨፋና በወጣቱ ላይ የሚያደርሰው ሥቃይ በህዝቡ ዘንድ የስነ ልቦና ተጽዕኖ ከመፍጠሩም በላይ በአካባቢው ነዋሪ ሊረሳ የማይችል ሀዘን ማስከተሉ ቀጠለ:: ይሄኔ ወጣቱም የትግሉን እሳት አፋፋመው::

በኢትዮጵያ የዕኩልነት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይስፈን!
የሰውል ልጅ ዘለዓለማዊ ሙበት ፍትህና ነጻነት ጽኑ ይሁን!
የመናገርና የመጻፍ ሙበት ይከበር!
የጉልተኛው ሥርዓት ተጠቂ የነበረው ገበሬ የመሬቱ ሙሉ ተጠቃሚ ይሁን!
ህዝባዊ መንግሥት ይቋቋም!

ወዘተ እያለ ወጣቱ ትግሉን ተያያዘው:: ደርጉም ግድያና ጭፍጨፋውን ቀጠለ:: ታጋዩም ለፍትህና ለዴሞክራሲ የሚያደርገውን ግስጋሴ እስከሞት ድረስ ተጋፈጠ::

እስከሞት ድረስ !!! በዚያች የሞትና የጣር ቀን በህይወቴ ሁሉ ከማልረሳቸው ታሪኮች ለዛሬ መስፍኔን ላስታውሳችሁ::

በወህኒ ቤቱ ውስጥ ካሉት እስረኞች የሚበልጠውን ቁጥር የያዘው የፖለቲካ እስረኛ ሲሆን ቁጥራቸው ከህምሳ በላይ ከሚሆኑት ውስጥ ሲሶውን የሚያህሉት ደሞ ሴቶች ናቸው::

ወደ ገፅ ፰ ዞሯል

# እኛው እራሳችን...

እኛው እራሳችን ካልቆምን ለመብታችን፤
እኛው ጥረን ግረን ካልፀዳ ቤታችን፤
ባእድ ምን ቸገረው ቢዘረፍ ቅርሳችን፤
ታሪክም ተንቋሾ ቢነቀል ስራችን ፤
ያልነበረው ቢኖር የነበር ቢጠፋ፤
ለሱ እስከደላው ጥቅሙን እስካስፋፋ።

እኛው በእኛ ሆነን፤ ቋሚና ማገሩ፤
ጉልላት ምሶሶው መቃኑና በሩ፤
መሰረቱን ጥለን ካልሰራነው ቤቱን፤
ላባችን ፈሶበት ጉልብት ተከስክሶ ቁንጮው ካልታሰረ፤
በባዕድ መሀንዲስ የማን ቤት ተሰራ! የማንስ አማረ?

ለኛ የሚበጀን እኛው ካላወቅነው፤
ሕዝባችን ሲበደል አለንህ ካላልነው፤
ባእድ ምን ሊበጀን እሮሮ ማብዛቱ፤
አምላክ እንዲምረን አንጋጦ ማየቱ!!
በዚህ ፈታኝ ጊዜ፤ ወግነን ካልቆምን፤
ዛሬ ትግልን ፈቅደን ነገን ካልፈጠርን፤
ወቅቱ ግድ ያለውን፤ ዛሬ ካልከፈልን፤

የሚተካው ትውልድ ፤ ምን ታሪክ ይኑረው?
አባት ካላቆየው ልጁስ በማን ይኩራ፤
የሚመጣው ትውልድ ምን አገር ይርከብ ምንስ ታሪክ
ያውራ?
ይበጃል ካላልን ግዑዝ ሆኖ መኖር፤
ክቡር ነው ካላልን ሥጋ ለብሶ ቆሞ፤ በታሪክ መቀበር፤
ይጥማል ካላልን መብት አልባ ህይወቱ፤
የራስ ግዳጅ ሸሽቶ በአበው መመካቱ፤
ሰው ህሊናን ሽጦ ለሆድ መገዛቱ፤

የህላዌን ሚስጥር በደንቡ ላጤነው፤
የሕይወት ጣእሙ፡ ኖሮ ማለፍ ሳይሆን አልፎም መኖሩ
ነው።
(ከስጉደታ) መርካቶ

# ያ ትውልድ ሲታወስ

(ቁጥር 1)

ከገፅ ፺ የዞረ

በወህኒ ቤቱ ውስጥ ለዘመናት ሲከወኑ የቆዩ ሥርዓቶችና ልማዶች አሉ:: ከነዛም ውስጥ ከቀኑ አሥራአንድ ሠዓት ሲሆን እስረኛው ወደየክፍሉ እንዲገባ ይደረጋል:: ከመግባቱ በፊት በየበራፉ ላይ ተሰልፎ ይቆጠራል:: ቆጠራው እንዳበቃም የጸሎት ሥነ ሥርዓት ይደረጋል:: ጸሎቱም የሚደረገው በኦሮምኛና በሲዳምኛ ሲሆን ከእስረኛው መሀል ትልቅ በሚባሉና በተመረጡ ሽማግሌዎች ይሆናል:: ወቅቱ የምርመራና የስቃይ ወቅት ነበር:: በጠዋት የተወሰዱት ልጆች ቀን ላይ ካልተመለሱ ኃይለኛ ሥቃይ እየደረሰባቸው መሆኑን እናውቃለን::

በጠዋት ለምርመራ የተወሰዱ ልጆች ፲፩ ሰዓት ሆኖ ወደየክፍላችን እስከምንገባ ድረስ አልተመለሱም:: ቀኑን ሙሉ በፍርሀትና በመሸበር ነው ያሳለፍነው:: በየክፍላችን ከገባን በኋላ ጀንበር ዘቅዘቅ ስትል ከውጪ ድምጽ ተሰማን:: ወዲያው በክፍላችን ውስጥ ጸጥታ ሠፈነ:: በራችን ተከፍቶ ሁለት ልጆች ወደክፍሉ ተጣሉና ተመልሶ ተከረቸመ:: አድማሱ ነፍሱን አያውቅም ...ፍጹም ደክሟል:: ኩራዙን ጠጋ አድርገን ስንመለከተው የለበሰው ስስ ሸሚዝ በጉማሬው እራፊ ከሰውነቱ ጋር ተጣብቋል:: እግሩ በእሳት ታቃጥሎ ጣቶች እንዳሉት እንኳ አያስታውቅም:: ጠረኑም ተለውጧል:: በደንብ ለማስተኛት ስናገላብጠው ከማቃሰት በስተቀር ምንም የሚያውቀው ነገር የለም:: ሲተነፍስ ቶሎ ቶሎ ስለነበር ሌሊቱን በሰላም ያድራል ብዬ መገመት አቅቶኝ ተጨነቅኩ:: ሁኔታውን ሳስተውለው ሰውነቴ ተረበሸ:: አለፍ አለፍ እያለ የሚያወጣውን የጣር ድምጽ የሚሰማ ማንም እንቅልፍ ሊተኛ አይችልም:: በክፍሉ ውስጥ ያለው እስረኛ ሁሉ በሀዘን ልቡ ተነክቷል:: ሌላው አሁን በህይወት ያለና እስከማውቀው ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚኖር በምን ሁኔታ እንደሚገኝ ደግሞ ስለማላውቅ ስሙን ከመጥቀስ እቆጠባለሁ... ሆኖም በህይወት ከተረፍነው ውስጥ ደግሞ እንደሱ ስቃዩን ያየ የለም ለማለት እደፍራለሁ:: እስርቤት ውስጥ ለወራት ያህል በጉልበቱ ሄዷል:: ምናልባት ይህቺን ጽሁፍ ቢያነብ ሊያገኘኝ ወይንም አስተያየት ሊሰጥ እንደሚሻ እገምታለሁ:: በክፍሉ ውስጥ ባለው የመኝታ ሥርዓት ሶስት ወደራስጌ ሶስት ወደግርጌ እየሆነ ሲሆን ከሶስታችን እኔ ከመሀል፣ አድማሱ አንዳርጌ እና አሁን በሎንዶን የሚኖር ጓደኛዬ በግራና በቀኜ ይተኛሉ::አልፎ አልፎ ማቃሰቱን ቆም ሲያደርግ ጣቶቻችንን ወደአፍንጫው ጠጋ እያደረግን ትንፋሹን እናዳምጣለን:: ሌሊቱን አብረነው በጭንቀት ሳለን እንዳይነጋ የለም የንጋት ብርሃን በሰቀላው መስኮት አልፋ እርስ በእርስ እንድንተያይ ፈቀደች::ይሄኔ አድማሱ ቃል ተነፈሰ ራሱን ቀና አድርጌ አድማስ አድማስ እያልን ደጋግመን ጠራነው:: ውሃ ሲል አሁንም ቃሉን ደገመ:: በክፍላችን ከሽንት እቃ በስተቀር ምንም ነገር የለም:: አንድ ሠዓት ሆኖ በሩ እስከሚከፈትልን ድረስ:: አድማሱ የእድገት በህብረት ዘማች የነበረ እና የ፲፪ኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን በፓርቲው ጠንካራ ዲሲፕሊን የታነጸ ለዲሞክራሲው ትግል ራሱን ሙሉ ለሙሉ የሰጠ ልበ ሙሉና ደፋር ወጣት ነበር::

ይህ ሁሉ ሲሆን በሌላ ክፍል ውስጥ ያለው ጓደኛዬ መስፍን መሀመድን ለአፍታም ከጎሊናዬ አልለየሁትም:: ጠዋት አንድ ሰዓት ሆኖ የክፍላችን በሮች ተከፍተው እስካየው ድረስም ቸኩያለሁ:: ሰዓቲቱም ደርሳ በሩ እንደተከፈተልን ያለበት ክፍል ሮጬ ሄድኩና ከተጋደመበት ጎንበስ አልኩ ወደ ጆሮው ጠጋ ብዬ "መስፍኔ መስፍኔ ደህና ነህ?" አልኩት::

ዓይኖቹን መግለጥ ባይችልም ሰምቶኛል፤ አዎንታውን በሆነ እንቅስቃሴ ገለጠልኝ:: ወትሮም ከሲታ የነበረው ሠውነቱ ይባስ ገርጥቷል። በፖለቲካው ልጆች በነበርን ግዜ ዴሞክራሲያን ሀ ብለን ስንተዋወቅ ከመስፍን ጋር በአንድ ሴል ውስጥ እናጠና ነበር:: በባህሪው በጣም ዝምተኛና ቁጥብ ነው::

በእለቱ በጊቢው ጽዳት እንዳጸዳ ተመድቤ ረፋድ ላይ ስራዬን ጨርሼ ወደመስፍን ስመለስ፤ ዓይኖቹ ተገልጠው መናገርም ችሎ ነበር:: በእስር ቤቱ ወስጥ ትኋንና ተባይ እንዲሁም የክፍሉ ትንፋት ሌላው ችግር ስለነበር ወደውጭ እንድናወጣው ተነጋግረን ራሱን ሲያውቅ ሲነቃ "መስፍኔ" ብዬ ጠራሁት::ወደኔ ተመለከተና ፈገግ ሲል ለኔ ብቻ ሊገባኝ የሚችል መልክት እየሁና ጥንካሬ ተሰማኝ:: አፍጥጦ እየተመለከተኝ ለደቂቃዎች ቆየ::

መጀመሪያ ከህሊናው የፈለቀው ቃል መዝሙር ነበር:: በግርፋት የተላላጠ አካሉን እየደባበሰ ይዘምራል:: እኔም አብሬው መዘመር ጀመርኩ:: ዝም ሲል እኔም አብሬው ዝም አልኩ:: ድካም ነበረበትና በእጁ ምልክት እያሳየኝ ቀጥል አለኝ እኔም ቀጥዬ ዘመርኩ ድምጹ ወደውስጥ እንደሚናገር ነው የሚመስለው:: ጮክ እያልክ ዘምር እያለ በእጁ ምልክት ያሳየኛል:: ሆኖም እኔ መጮህ አልቻልኩም ...መናገር ቢችል ስቃዩን አምቆ ህመሙን በደስታ ለውጦ ለትግሉ ያለውን ጽናት እየዘመረ ሲገልጽ ታሰበኝና ሞት አይፈሬነቱ አስደነቀኝ::

እንዲህ ባለ ስቃይ ውስጥ ሆኖ ነሀሴ ፲፪ ቀን ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ዓመተ ምህረት ከሌሎች ፲፯ ወንድሞቻችን ጋር ተገደለ::

ወደ ገፅ ፬ ዞሯል

